# ዴሞክራሲያዊ የሥርዓት ለውጥ ስንል ለምንና እንዴት?

ጠገናው ጎሹ

December 23, 2017

እጅግ በጣም ቀላል በሆነ አገላለፅ ሥርዓት (system) የየራሳቸው ባሕሪና ተግባር ያላቸው አካላተ ሥርዓት (subsystms) ተደጋጋፊና መስተጋብራዊ ግንኙነት በመፍጠር ለአንድ ሙሉ (the whole) ሥርዓተ አካል (ነገር) ህልውና መሠረት የሚሆኑበት የማያቋርጥ ሂደት ነው።

ይህ ሂደት የአንድን ሙሉ ሥርዓተ አካል (the whole system) ህልውና ከማረጋገጥ አልፎ እንደአስፈላጊነቱም ለውጥና ዕድገትን ማስከተልና ማጎልበት ካለበት ሁሉም ክፍለ አካሎቹ (subsystems) የየድርሻ ተግባራቸውን በተገቢው መንገድ የማከናወን ዝግጁነታቸውና ብቃታቸው አስፈላጊነት ፍፁም ነው። ይህ ለህልውና እና ለጤናማ ለውጥ እውን መሆን ፍፁም አስፈላጊ የሆነ ሂደት በአንድ ወይም በሌላ ምክንያት ወደ ተሻለ የለውጥ እርምጃ መራመድ ይቅርና  የሥርዓተ አካሉን (the whole system) ህልውና እንዳለ ለማቆየት ቢሳነው የሚከተለው ውጤት  ምን ያህል አስከፊ እንደሚሆን ለመገንዘብ የጤናማ አእምሮ እና አስተሳሰብ ባለቤት መሆን ብቻ በቂ ነው።

ሥርዓተ ፀሐይ (solar system) የተለመደውን ኡደታዊ ተግባር ማከናወን ቢሳነው ሊያስከትል የሚችለውን ውጤት ማሰብ የሚቻለው ምንም እንኳ የሚሆንበትን የዘመን ቀመር እና ሰዓቱን በትክክል መተንበይ የሚቻል ባይሆንም ሁሉም ነገር እንደነበረ እንደማይኖር  ሳይንሱ የሚነግረንና ሃይማኖታዊ እምነትም(religious belief) ምፅዓተ ዘመን ብሎ የሚጠራውን ኩነት ብቻ ነው ። ይኸ ከሰው ልጅ ዕውቀትና አቅም በላይ የሆነ የሥርዓተ ተፈጥሮ ለውጥ «እኔ እያለሁ አይሁን እንጅ ለሌላው ግድ የለኝም» የሚል ዓይነት አስተሳሰብ ( mentality) ያለው ሰብአዊ ፍጡር የሚኖር ከሆነ ቢያንስ ባለ ጤናማ አእምሮ አይደለም ሲከፋ ደግሞ በሌሎች ወገኖቹ ሰቆቃ የሚደሰት (sadist) መሆን አለበት።

የአካላችን ግድግዳና ምሰሶ የሆነው ሥርዓተ አጥንታችን (skeletal system) ፣ የሱው መለሰኛ የሆነው ሥርዓተ ጡንቻችን (muscular system) ፣የስሜት እና የመልእክት ማስተላለፊያ ሥርዓታችን (nervous system)፣ ከሌሎች እንስሳት የላቅን ያደረገን አእምሮአዊ ሥርዓታችን (brain system) ፣ የምግብ ማድቀቂያና ማዋሃጃ ሥርዓታችን(digestive system) ፣አየር መውሰጃና ማስወገጃ ሥርዓተ እስትንፋሳችን (respiratory system) ፣ የደምና ሌሎች አስፈላጊ ፈሳሾች ሥርዓተ ዝውውራችን (circulatory system) ፣  የማይፈለጉ ነገሮችን የማስወገጃ ሥርዓታችን ( excretion and urinary systems)፣ ወዘተ ያላቸው መስተጋብራዊ ግኑኝነት ነው ሰው የመሆን ህልውናችን ዕውን የሚያደርገው። ይህ መሠረታዊ የተፈጥሮ ሥርዓተ ሰውነታችን (human system) በእኛው በራሳችን ወይም ከእኛ አቅም በላይ በሆነ ምክንያት ቢስተጓጎል የሚያስከትለውን አስከፊ ውጤት "በእኔ ላይ  ካልደረሰብኝ ህመሙ ጨርሶ  አይሰማኝም " ወይም "ምንስ ቢሆን እኔ ደህና እንጅ  ምን አገባኝ" የሚል ሰብአዊ ፍጡር ካለ እርሱ እራሱ የታማሚ ሥረዓተ አእምሮ ጉዳተኛ ወይንም የእራሱን ምንነት (ሰው መሆን) ጨርሶ የማያውቅ ወይም ማወቅ የማይፈልግ በስሙና በሥጋው ብቻ ሰው የተሰኘ እንስሳ መሆን አለበት።

ለአያሌ ዘመናት የመጣንበትን የዴሞክራሲያዊ ነፃነት አልባ ሥርዓተ ማህበረሰብ ታሪካችን እና በተለይ ግን አሁንም እየዘረፉ፣ እያዋከቡ ፣እያዋረዱ ፣ እየቀጠቀጡ (እያሰቃዩ) ፣ በየማጎሪያ ቤቱ እያገቱ ፣ እና ሲያሻቸውም እየገደሉ "የሕዝባዊ ሥርት በረከቶች " ነን እያሉ የሚሳለቁብንን ገዥ ቡድኖች ኢሰብአዊ ባህሪቸውንና ድርጊታቸውን ጥልቀትና ስፋት ለማሳየት እንደመግቢያ ይህን ያህል ካልኩኝ ወደ ዋናው ርዕሰ ጉዳዬ ልለፍ።

የሰው ልጅ ከሌሎቹ እንስሳት በተሻለ ነገር ግን በዘፈቀደ ወይም ፍላጎቱ እንዳስገደደው እየተንቀሳቀሰም ቢሆን መሠረታዊ የተፈጥሮ ፍላጎቱን ለማሟላት ከሚባዝንበት እርሱነቱ በመውጣት ቤተሰብ(family) ከምንለው መሠረታዊ ተቋም አልፎ እንደማህበረሰብ (soceity) መኖር ሲጀምር ይሁኑ አዲስ ፣ ባለብዙ ፍላጎትና ውስብስብ ኩነት (reality) የሚያስተናግድ ሥርዓተ ማህበረሰብ የማበጀቱ አስፈላጊነት ውዴታም ግዴታም ነበር ::  አሁንም ነው።  ውዴታነቱ በሚኖርበት ሥርዓተ ማህበረሰብ ማዕቀፍ ሥር ፈቅዶና በሙሉ ነፃነትና መብት ተሳታፊ ሆኖ የመኖሩ ፋይዳ ለእያንዳንዱም ሆነ ለሁሉም  አማራጭ የሌለው መሆኑን አምኖ የሚያደርገው ሲሆን ፣ ግዴታነቱ ደግሞ ይበጀኛል ያለው ሥርዓተ ማህበረሰብ የተመሠረተባቸውንና የሚመራባቸውን ሥርዓተ መረሆዎችና ሕግጋት እንዲሁም ያልተፃፉ ግን እጅግ አስፈላጊ የሆኑ ማህበራዊ ፣ ሞራላዊ ፣ ሥነ ምግባራዊ እና የሃይማኖታዊ እምነቶች (religious beleifs) እሴቶችን  የማክበርና የመጠበቅ አስፈላጊነትን አምኖ መቀበል ነው።

የዕድገት ሂደት ህግ ነውና ዘመን በተቆጠረ ቁጥር የሰው ልጅ ህልውናውን ለማረጋገጥ (ለማስቀጠል) ብቻ ሳይሆን የአኗኗር ፍልስፍናውንና ዘዴውን ለማበልፀግ በሚያደርገው የማያቋርጥ የትግል ሂደት የእራሱን ከየትነትና ወዴትነት እና እንዲሁም የአካባቢውን ምንነትና እንዴትነት ይበልጥ በተረዳ መጠን የቆመበት ሥርዓተ ማህበረሰብ በመጠን እየገዘፈ፣ በይዘትም እየተወሳሰበ መሄዱ አይቀሬ ነው። ይህን ሥርዓተ ማህበረሰብ እንደ አንድ ነባራዊና ዕድገቱ የማያቋርጥ ህልው አካል ( living and growing body) በመስተጋብራዊ ግኙኝነታቸው የተሟላ የሚያደርጉት የፖለቲካ ፣ የኢኮኖሚ ፣ የማህበራዊ ፣ የሞራል እና መንፈሳዊ ክፍለ አካሎቹ  (subsystems) ናቸው።

አንድ ማህበረሰብ እንደ ማህበረሰብ ህልውናውን ለማረጋገጥ ብቻ ሳይሆን ጤናማ የለውጥ (የዕድገት) ጉዞውን የተቃና ያደርግልኛል ብሎ የጠበቀው (የሚጠብቀው) ሥርዓተ ማህበረሰብ (societal system) የእኔ በሚላቸው ወገኖቹ ቁጥጥር ስር ወድቆ ለዘመናት የመከራና የውርደት ምንጭ ሲሆን ሊያስከትል የሚችለውን ብርቱ ጉዳት ለመረዳት ከእኛ ከእራሳችን የበለጠ ማስረጃ የሚኖር አይመስለኝም።

አዎ! የራሳቸውን ፍላጎትና ጥቅም ማስፈፀሚያ ሥርዓት አዘጋጅተው፣ ዘርግተውና ለተፈፃሚነቱም በማያቋርጥ የማቴሪያልና የገንዘብ ፍሰት እና ርህራሄ እንዳይኖረው አድርገው ባሰለጠኑት የሰው ኀይል አስታጥቀው አገርንና ወገንን ለሩብ ምዕተ ዓመት ታይቶ በማይታውቅ ሁኔታ የመከራና የውርደት ተሸካሚ አድረገውታል። ሲያስፈልጋቸው "ከእኛ መልካም ፈቃድ ውጭ ወዮልህ !" ብለው የተጠንቀቅ አዋጅ እያወጁ ፣ ሲያሻቸው ደግሞ "የእኔን ያየህ ተቀጣ" ሰይፋቸውን እየመዘዙ የሚገዙ ገዥዎችን በዚህ ዘመን ተሸክሞ መኖር  ህመሙ ምን ያህል የከፋ እንደሆነ ለመረዳት ገላጭ ቃላት ፍለጋ መድከም ያለብን አይመስለኝም።  አዎ! እንኳንስ ለእኛ ለእራሳችን ለማነኛውም በቅንና ሚዛናዊ አእምሮ ለሚያይና ለሚያስብ ሰው ምስቅልቅሉ የወጣው የሕዝብ ሁለንተናዊ አኗኗር እና በታሪካችን አጋጥሞን የማያውቅ ብሔራዊ ውርደታችን ገዝፎ የሚታይ መሪር ዕውነታ ነው።

በተለይ እንደኛ ላለ እንደማነኛውም የታሪክ ሂደት ከነችግራችንም ቢሆን የረጅም ጊዜ አኩሪ ታሪክና ባህል ባለቤቶች ነን ብሎ ለሚኮራ ህዝብ እንዲህ ዓይነት የመከራና የውርደት ሥርዓተ ማህበርሰብን ሩብ ምዕተ ዓመት ሙሉ  ተሸክሞ  የመዝለቁ ነገር የምንኮራበትን ከወዴትነታችንና ማንነታችን (ኢትዮጵያዊነታችን) አልተፈታተነንም እያልን ለራሳችን እየነገርነው ከሆነ እራሳችን እያታለልነው ነውና ለራሳችን ዕነቱን ነግረን በዕውነት ነፃ እንውጣ።   የመከራ ህይወትና ብሔራዊ ውርደት ለሚያመው የአገሬ ሰው መዳኛው መንገድ ይኸው ብቻ ነው።

ይኸውና አሁንም  የመንግሥትነቱን መዘውር ሲያመቻቸው በቀጥታ ሳይመቻቸው ደግሞ በተዘዋዋሪ የሚዘውሩት የህወሃት የበላይ አለቆች የግድያ ፖለቲካቸው  የሕዝብን እምቢተኝነት አላስቆም ሲላቸው ጠፍጥፈው የፈጠሯቸውንና አሰልጥነው ያሳደጓቸውን  ካድሬዎቻቸውን (ብአዴን/ኦህዴድ/ደህዴን ) አሰማርተው የሚያካሂዱትን ሕዝብን የማቄል (የማታለል) ዘመቻ ተያይዘውታል። ይህን የሥልጣን ዕድሜ ማራዘሚያ ዘመቻ  አንዳንዶቻችን መሠረታዊ የሥርዓት ለውጥ ጥያቂያችን እስከሚፈታተን ድረስ "አወንታዊና ልብ የገዛ ዘመቻ"እስከማለት መሄዳችን ለዘመናት የታመምነውን ብርቱ የፖለቲካ ህመም ነቅሎ የሚጥል መድሃኒት (መሠረታዊ የሥርዓት ለውጥ) ዕውን የማድረግ ጥረታችን ያኮሰምነዋል እንጅ አያጎለብተውም።  ስለሆነም በትክክለኛ መፍትሄ ፍለጋው (ክፉውን ሥርዓት በበጎ ሥርዓት የመተካት) ጥረታችን ላይ መረባረብ ይኖርብናል። በዕውን ፈውስን የምንፈልግ (የምንናፍቅ) ከሆነ ።

የገዥውን ቡድን የአፈና እና የግድያ ሥርዓት ለማስወገድና ዕውነተኛ ዴሞክራሲዊ ሥርዓት ለመመሥረት መታገል  ቀላል እንዳልሆነ እየሰማነው ሳይሆን እየኖርነው ያለ እውነታ ነው ። በሌላ በኩል ግን እምቅ አቅሙ ሳያንሰን ባለመተባበር ብቻ ሳይሆን በመጠላለፍ ክፉ አባዜ ተለክፈን (እራሳችን በራሳችን አስለክፈን) በተጫነብን የመከራና የውርደት ሥርዓት ሥር ለዘመናት እያለቀስንና እየተላቀስን የመኖራችን ነገር  ከእኛው ከራሳችን ሁለንተናዊ ውድቀት (በአብሮነትና በቁርጠኝነት ለመቆም አለመቻል) በስተቀር ሌላ ምንም አይነት አሳማኝ ምክንያት የለውም። ለዚህም ነው "የባለጌና ጨካኝ የገዥ ቡድኖችን የሥልጣን ዕድሜ ለሩብ ምዕተ ዓመት ያራዘምንላቸው እኛው ነን" የሚለው ትክክለኛ የሆነ እራስን የመጠየቅና የመመርመር ድፋርነት የሚሆነው።

የዛሬ መቶ ስድሳ ሶስት አመት ነበር አፄ ቴዎድሮስ "ትልቅ ነበርን ወደፊትም በአንደነት ትልቅ እንሆናለን!"ያሉት። በዚያ ሥልጣኔያችን ከጥንታዊነት ባላለፈበት ዘመን ከወቅቱ የንቃተ ህሊና እና ነባራዊ ሁኔታ አንፃር ሊተነተንና ሊተች የሚገባው ጥፋታቸው እንዳለ ሆኖ እንደዚያ ዓይነት ራዕይ (vision) የነበራቸው አያትና ቅድመ አያቶቻችን ዛሬ ቀና ብለው "ያለምንላችሁና ያሳየናችሁ የትልቅነት ማንነት የት ደረሰ? እንዴትና ለምን ?" ብለው ቢጠይቁን ምን ልንል እንደምንችል እራሳችን ብንጠይቅ በቀላሉ የምንመልሰው አይመስለኝም። ስለሆነም  ከስሜትዊነት ወጥተን አወንታዊ እና አሉታዊ የታሪክ ጉዟችን በአስተማሪነቱ ፣ ዛሬ ያለንበትን ዕውነት በወሳኝነቱ ፣ የቀጣይ (የነገ) ጉዟችን የበለጠ ስኬታማነቱን አይይዘን የምንረዳበት ፣ ወደ እሚጨበጥ የዕድገት(ልማት) ኀይል የምንለውጥበትና ለትውልድ የምናስተላልፍበት የዕውቀትና የሞራል ጀግንነት ግድ ይለናል ። ያለዚያ የእነዚያን አየቶቻችንና ቅድመ አያቶቻችን ገድል "ከመቃብር

ተነስታችሁ ይህችን አገር እንደራዕያችሁ የምንኖርባት ምድር ካላደረጋችሁልን እኛስ አልሆነልንም" የሚል አንድምታ ባለው ጥሪ በየዘፈኖቻችን ፣ በየመዝሙሮቻችን (ዓለማዊ ወይም መንፈሳዊ) ፣ በየቀረርቶና ፉከራዎቻችን ፣ በየተውኔተ ትረካዎቻችን እና በየእግዚኦታ ፀሎታችን ብቻ እያስተጋባን መሠረታዊ የሥርዓት ለወጥ ማምጣት ይቅርና የገዥዎቻችን ገደብ የለሽ የጭካኔ በትርን ለማስታገስ መቻላችንም ቅዠትነት ካልሆነ በስተቀር ዕውነትነት አይኖረውም።
ስለአንድ ሥርዓተ ማህበረሰብ ውድቀት ወይም ስኬት ስንነጋገር የፖለቲካ ሥርዓቱ ምንነት፣ ለምንነት ፣ እንዴትነት እና ለማንነት ቀድመው የሚመጡ ጥያቄዎች ናቸው ። ይህም ያለምክንያት አይደለም። የፖለቲካ ሥልጣን ስንል የአገር ሃብት (resource and wealth) እንዴት ይሰራጫል (ይከፋፈላል)? በማህበረሰቡ ውስጥ ማን ምን ቦታ አለው ? ማን ምን ማግኘት አለበት ? እንዴት፣ መቼና የት ማግኘት አለበት ? የፖሊሲ አውጭነትና የውሳኔ ሰጭነት ሥልጣን (policymaking and decision- making authority) ያለው ማነው? የውሳኔው ምንጭ ፣ አካሄድ ፣ አወሳሰንና ተግባራዊነት ፋይዳው( ጠቀሜታው) ለምንና ለማን ነው ? የሚሉና ሌሎች በርካታ ተያያዥ ቁልፍ ጉዳዮች (ጥያቄዎች) እንደየ ሥርዓት ማህረሰቡ ባህሪና ዓላማ የሚስተናገዱበት ሥርዓት ነው ።ለዚህ ነው የሰብአዊ መብት ልዕልናን ፣ የማንነት ክብርን ፣ የፍትህና የነፃነት ዋጋን ፣ የሰላምና የፍቅር ፋይዳን እና የጋራ ብልፀግና ኅያልነትን ከምኞት ያለፈ ዕውን የምናደርግበት የፖለቲካ ሥርዓት ለውጥ ግድ የሚለን ።
የአንድ ማህበረሰብ የፖለቲካ ሥርዓት ህዝባዊና ዴሞክራሲያዊ መሆን ወይም አለመሆን የስኬት ወይም የውድቀት ዓይነተኛ ምክንያት ነው ። ለዚህ ነው "እኔ ስለፖለቲካ ምን አገባኝ?" ስንል ምን ማለታችን እንደሆነ እራሳችንን መልሰንና መላልሰን መጠየቅ ያለብን ። ለዚህ ነው "እኔ ስለሃይማኖት እንጅ ስለ ፖለቲካ ሥርዓት ምን አገባኝ"ስንል የአገርና የወገን መከራና ውርደት አያገባኝም እየልን መሆኑን ልብ ማለት ያለብን። ለዚህ ነው ወገንና አገርን የውርደትና የመከራ ማቅ ያከናነበውን ሥርዓት በድርጊት አልባ ጸሎትና እግዚኦታ አስወግደን ደግ ዘመን ይመጣል የሚለው ስብከታችን ከገዥዎች ያልተናነሰ አደንቋሪና የግፍ ሥርዓተ ማህበረሰብ ዕድሜ አስቀጣይ የሚሆነው።
ክርስቶስ በቁሙም ሆነ በመስቀል ላይ እንኳን ለማየት ለመስማትም የሚያስቸግር ስቃይና መከራ የተቀበለው በዋናነት በዚህች በምድራችን እያለን ለፍትህ ፣ ለሰላም ፣ ለፍቅር ፣ ለሰብአዊ ክብር ፣ ወዘተ የምንከፍለው ተመን የማናገኝለት መስዋዕትነት (priceless sacrifice) ለወዲያኛው ዓለም መግቢያ ነው ብሎ ሲያሳየን ነው እንጅ ስቃየን ፣ ሞቴንና በኋላም ትንሳኤየን በማመናችሁ ብቻ ትድናላችሁ ያለበትን መጽሐፍ ወይም ዝክረ ክርስትና በበኩሌ አላነበብኩም ። መጽሐፉን ወይም ዝክረ ክርስትናውን የምንተረጉምበት የፍላጎት እና የአቅም (intention and ability) ልዩነት እንዳለ ሆኖ ። ለዚህ ነው ክርስቶስ የፍትህ አልባና የግፍ ገዥዎችን (የሥልጣን ባለጌዎችን) ተፀይፎ ፣ አወግዞ እና በመጨረሻም ለዕውነተኛ ፍትህ ፣ ፍቅርና ሰላም ሲል ስቃይና መከራ ተቀብሎ መስቀል ላይ መዋሉን በአፋችን እያነበነብን በድርጊት ግን ከገዳዮቹ ብዙም የተሻልን አለመሆናችን እየመረረንም ቢሆን ተቀብለን ወደ ትክክለኛው የህይወት መንገድ መመለስ ያለብን።
ሃይማኖታዊ እምነትን ከተግባር (ለሰብአዊ መብትና ክብር እስከ መስዋዕትነት የመሄድን አስፈላጊነት) ነጥሎና በየቤተ እምነቱ መሽጎ የሚደረገው እግዚኦታ ባዶ ጩኸት ፣ ቅዳሴውና ውዳሴውም ይይስሙላ ፣ መነባንቡና ዝማሬውም ህይወት አልባ መሆኑን አምነን መቀበል ባንፈልግም መሪሩን ሃቅ ግን ደፍረን እስካልተጋፈጥነው ድረስ ሲተናነቀን ይኖራል ። እናም የእስከአሁኑ ይበቃልና የአገርና የወገን መከራና ውርደት ያበቃ ዘንድ ለሚበጀን የሥርዓት ለውጥ ነገ ሳይሆን አሁንኑ ሳናውቅም ሆነ እያወቅን ከተዘፈቅንበት የአስተሳሰብና የድርጊት ድህነት ለመውጣት ፈቃደኝነቱና ድፍረቱ ይኑረን።
እንዲህ ሆነንና አድርገን የተገኘን ዕለት ነው መከራና ብሔራዊ ውርደት ያከናነበንን የፖለቲካ ሥርዓት አስወግደን መንበረ ሥልጣን ላይ የተቀመጠ ሁሉ የየራሱን የጭቆና እና የምዝበራ መረቡን የማይዘረጋበት ሕዝባዊና ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት የምንመሰርተው። ገና ዘመንና ሁኔታ ያልፈታው ብርቱ ችግራችን ተከብረንና በልፅገን የምንኖርበትን ሥርዓት አጥብቀን እየተመኘን ምኞት ወደ የሚጨበጥ ዕውነትነት ከሚለወጥበት የድርጊት (የትግል) ሜዳ ላይ ስንወርድ ያለመተባበራችን እንቆቅልሻችን ነው። እናም እርስ በርሳችን በግልፅ ወይም በስውር እየተጠላለፍን መልሰንና መላልሰን ወደ ነበርንበት ብቻ ሳይሆን ከዚያም በታች የምንወርድበት አስቀያሚ የፖለቲካ ባህላችን ተሸክመን የሚበጀንን የሥርዓት ለውጥ ማምጣት ከቶ የሚታሰብ አይደለምና ትግላችን መብታችን ከረገጡብን ጋር ብቻ ሳይሆን ከእራሳችንም ጋር ይሁን።።
ለመሆኑ ሕዝባዊና ዴሞክራሲያዊ የፖለቲካ ሥርዓት ለወጥ ስንል ምን ማለታችን ነው? በዚህ ጥያቄ ዙሪያ የሃሳብ ልውውጥ (ውይይት) ማድረግ አሁን በመካሄድ ላይ ያለውን ሕዝባዊ የእምቢተኝነት ንቅናቄ ለማገዝ ብቻ ሳይሆን እየታገልንለት ያለው ሥርዓተ ማህበረሰብ ምን አይነትና ለምን መሆን አለበት ? የሚለውን እጅግ ቁልፍ ጥያቄንም ለማንሸራሸር ይጠቅማል የሚል እምነት አለኝ። ከዚህ መሠረተ ሀሳብ በመነሳት ነው ሃሳቤንና አስተያየቴን እንደሚከተለው የማቀርበው።

ሕገ መንግሥት (constitution) የአንድን አገር የመንግሥት ዓይነት ፣ ቅርፅ ፣ ይዘት ወይም ሥልጣንና ተግባር የሚደነግግ ፥ በሕዝብና ሥርዓቱን በሚመራው (በሚያስተዳድረው) አካል መካከል የሚኖረውን ግንኙነት የሚወስን ፥ የመንግሥት ሥልጣንና

ተግባር ምንጭ ሕዝብ በመሆኑ በአፈጻጸም ሂደት ውስጥ በማናቸም ምክንያት የሥልጣን ምንጭ የሆነው የሕዝብ ልኡአላዊነት (sovereignty of the people) እንዳይደፈር ሥልጣን ላይ በሚቀመጠው አካል ላይ ገደብ የሚጥል ፥ የአገር የግዛት አንድነት (territorial integrity ) አይደፈሬነትን በዓለም አቀፍ ህግ መሠረት የሚያረጋግጥ ፥ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ እሴቶችን ፣ መረሆዎችንና ግቦችን በአጭሩና በግልፅ የሚያስቀምጥ ፥ የሃብት አጠቃቀምንና ክፍፍልን በግልፅና በማያሻማ አገላለፅ የሚያስቀምጥ ፥ የአገርን የተፈጥሮ ሃብት (natural resources) ባለቤትነትን ፣ አጠባበቅን እና አጠቃቀምን የሚገልፅ ፥ ዓለም አቀፍ ግኑኙነት (የሁለትዮሽም ይሁን ከዚያ በላይ) የአገርን ጥቅምና ደህንነት በሚያስጠብቅ እና በሚያጎለብት አኳኋን መሆን እንዳለበት መርሆዎችን በግልፅ የሚያስቀምጥ የሁሉም ህጎች ምንጭ ወይም የበላይ የህግ (supreme law of the land) ነው ።

ይህን የህገ መንግሥት ምንነት፣ ለምንነትና ለማንነት ለማነሳው ሃሳብና ለምሰነዝረው አስተያየት መነሻ ያደረግሁት ገዥዎቻችን የዛሬ 22 ዓመት (1988 ዓ.ም) አፅድቀው ሥራ ላይ ያዋሉትና ሲፈልጉ ማታለያ ሲያሻቸው ደግሞ መቅጫና መቀጣጫ ያደረጉት ህገ መንግሥታቸውን ከምር ልብ እንበለው ለማለት ነው። ምክንያቱም የመከራና የውርደታችን ቁልቁለት የሚጀምረው ከዚሁ ለእኩይ ፖለቲካ ማስፈፀሚያነት ከዋለው "የህጎች ሁሉ የበላይ ህግ" በመሆኑ ነው።

የሪዕሰ ጉዳዬን መሠረተ ሃሳብ በቀላሉ ለማግኘትና ለመረዳት ይረዳ ዘንድ ሃሳብና አስተያየቴን እንደሚከተለው ላቅርበው ።

1.ህገ መንግሥት የአገርና የህዝብ ፍላጎትና ጥቅም ዕውን የሚደረግበት መሳሪያ ወይም የገዥዎች (አምባገነኖች) ፖለቲካ ጨዋታ (ድራማ) ሰነድ መሆን አለመሆኑን ከሚወስኑት ሁኔታዎች አንዱና ዓይነተኛው በሶስቱ የመንግሥት አካላት ማለትም በህግ አውጭው/ፓርላማው ፣በህግ አስፈፃሚው/አስተዳደሩ እና በፍትህ አካሉ/የአቃቤ ህግና የፍርድ ቤት ሥርዓቱ መካከል የሚኖረው የሥልጣንና የተግባር ግኑኝነት ነው።

የአገራችን ፓርላማ የሥራ አስፈፃሚውን (የአስተዳደሩን) በትረ ሥልጣን የጨበጡ ፣ የገዥውን ፓርቲ በበላይነት የሚመሩ ፣ የጦርና የፀጥታ ኅይሉን በጠቅላይ አዛዥነት የሚቆጣጠሩ ጎሰኛ (ዘረኛ) ባለሥልጣናት የህዝብ ተወካዮች በሚል ስም ወይም ሽፋን ሲፈልጉ በተፃፈ አዋጅ ሲሻቸው ደግሞ እጅ በማስውጣት በፀደቀ ቃለ ጉባኤ የገደብ የለሽ ሥልጣናቸው ሥጋት መስሎ የታያቸውን ቢችሉ የሚያታልሉበት ይህ ካልሠራ ደግሞ አይቀጡ ቅጣት የሚቀጡበትን መሣሪያ (instrument) የሚፈበርኩበት ክፍል (chamber) ነው።ይህ ኢህአዴግን በጭፍን ለማጥላላት ወይም በሃሰት ለመወንጀል የሚባል አባባል ሳይሆን የኢትዮጵያን ህዝብ ለሩብ ምዕተ ዓመት በእጅጉ የፈተነ መሪር እውነት ነው ።

እስኪ ይህን እጅግ መሪር ዕውነት ለሚከተሉት ጥያቄዎች በዕውነት ስለዕውነት ከምንሰጠው መልስ አኳያ የየራሳችን ህሊና ምን እንደሚለን ከምር እናዳምጠው ፥

•ሦስቱ አካላት በተቀመጠላቸው መርህና ህግ መሠረት ሥልጣናቸውን ተጠቅመው ኀላፊነታቸውን በዕውን ይወጣሉ ወይስ ህግ አውጭውና ህግ ተርጓሚው የህግ አስፈፃሚው የፖለቲካ ጨዋታ አሻንጉሊቶች (playhoses) ናቸው?

•ሶስቱም በተቀመጠላቸው የሥልጣን ክፍፍል እና ሥልጣን በአንደኛው ተፅዕኖ ሥር እንዳይወድቅ በሚያስችል (separation of power and, check and balance) መርህ መሠረት ኀላፊነታቸውን ይወጣሉ ወይስ ከስምና ለገዥው ፓርቲ የካድሬ ሠራዊት የሥራ ዕድል (እድል ከተባለ) ፈጣሪ ከመሆን አልዘለሉም?

• በህዝብ ለህዝብ ተመርጠ የሚባለው ፓርላማ በዕውን የህዝብ ተጠሪነቱን የሚያረጋግጡ ተግባራትን ያከናውናል እንዴ ?

•የአስፈፃሚውን አካል አሰራር ህጋዊነት ከህዝብ ደህንነትና ጥቅም አንፃር በዕውን ይከታተላል እንዴ?

•የሚቀርብለትን የአስፈፃሚውን አካል መደበኛም ይሁን ልዩ የአፈፃፀም ሪፖርት በጥንቃቄ ተረድቶ የህዝብ ፍላጎትና ጥቅምን መሠረት ባደረገ አኳኋን ስኬትንና ድክመትን በመገምገም ተገቢውን እርምጃ ይወስዳል ወይስ ሪፖርት አቅራቢውን (ፕሬዝደንት ወይም ጠቅላይ ሚኒስትር) አሞግሶ ለማፅደቅ ወይም ተቀብየዋለሁ ለማለት እጅ የማዉጣት ስብሰባ ላይ ይቀመጣል ??

•የአገር ሉአላዊነትና የግዛት አንድነት ሲደፈርና ዜጎች ድንበር ተሻጋሪ በሆኑ ወንጀለኛ ቡድኖች ወይም በጎረቤት አገር ወታደሮች (ታጣቂዎች) ሲዘረፉ ፣ ሲገደሉና ታፍነው ሲወሰዱ የህግ አስፈፃሚውን መሪ ( ፕሬዝደንት ወይም ጠቅላይ ሚኒስትር እና የጦር ኋይል ጠቅላይ አዛዥ) በኀላፊነት ጠይቆ ተገቢውን እርምጃ ይወስዳል ?

•ህገ መንግሥታዊ የሰብአዊና ዴሞክራሲዊ መብቶችን ተግባራዊነት ዕውን የሚያደርጉ ሁኔታዎችን ያመቻቻል ወይስ መንግሥታዊ አሸባሪነትን በፀረ ሽብር ህግ ስም እያወጀ አገርና ህዝብ ያሸብራል?

•ዕውነትን በጢሙ የደፋን ሪፖርት "ከቡርነትዎ ለአቀረቡት ጥልቅና ሰፊ ሪፖርት ያለኝን አድናቆት እየገለፅኩ ሪፖርቱን እንደምደግፍ ስገልፅ ከአክብሮት ጋር ነው" በማለት እንደ ቃለ መሃላ በአንድ ዓይነት ቋንቋ በየተራ እያነበበ ሲምልና ሲገዘት ትንሽም ሃፍረት (ውርደት) የማይሰማው የፓርላማ አባል እንዴት ነው ከህዝብ የተቀበለውን ሥልጣንና ኀላፊነት ዕውን

የሚያደርገው?

•የሥራ አስፈፃሚውና የአገሪቱ መሪ (ጠቅላይ ሚንስትር) በየጎረቤት አገሩ በሰላም አስጠባቂነት ስም ወይም እንደአልሸባብ ያሉ አሸባሪዎችን ለመዋጋት በሚል በወጡበት የቀሩት የአገሪቱ ወታደር ዜጎችን ሁኔታ በሚያቀርበው ሪፖርት አለማካተቱ ስህተት እንደሆነና እንዲያብራሩ በወቅቱ የተቀዋሚ ፓርቲ አባል በነበረ የፓርላማ አባል ሲጠየቁ "ይኸ እናንተን(ፓርላማውን) አይመለከትም ፣ የማቅረብ ግዴታም የለብኝም" ብለው ኮስተር ሲሉ ወንበሩን የሞሉት አሻንጉሊት የካድሬ አባላት እንኳን ለምንና እንዴት ብለው ሊጠይቁ "ይህን ፀረ ሰላም ተቀዋሚ ልክ ልኩን ነገረልን" በሚል ዓይነት ሲያሽሟጥጡ እንዴት የህዝብ ወኪሎች እንበላቸው?

•በስህተት ወይም ሆን ተብሎ የህገ መንግሥት አተረጓጎም ችግር ቢከሰት ሙያዊ ብቃት ያለውና ከፖለቲካ አሻንጉሊትነት ነፃ የሆነ አካል መሆኑ ቀርቶ የህግ አስፈፃሚው (የጠቅላይ ሚንስትሩና ካቢኔው) የፖለቲካ ጨዋታ አሻንጉሊት ክፍል (playhouse) የሆነው የፌደሬሽን ምክር ቤት በሆነበት አገር የህዝብ መከራና ውርደት እንዴት ይቆማል? ፍትህና ርትዕስ በየት በኩል ዕውን ይሆናሉ ?

እናም ለዚህ ነው መፍትሄው ብርቱ በሽታ የሚያስከትለውን የህመምን ስሜት በጊዜአዊነት የማስታገስ ልማድ ሳይሆን (ያውም ከታገሰ ነው) በሽታውን ነቅሎ ማስወገድና አዲስና ጤናማ (ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት) መመሥረት የግድ ነው ማለታችን ዕውነት የሚሆነው ።

የሦስተኛው የመንግሥት አካል (branch of government) የፍትህና የፍርድ ቤት ሥርዓቱ ነው። የዚህ አካል ተልኮ ፣ ሥልጣንና ተግባር የህግ የበላይነትና የፍትህ አተረጓጎም በህገ መንግሥቱና በሌሎች ህጎች ከተቀመጠለት መርህና ዓላማ ጋር መሄዱን ወይም አለመሄዱን የማረጋገጥና ተገቢው የእርምት እርምጃ እንዲወሰድ ማድረግ ነው። ይህ ታላቅና ክቡር ሥልጣንና ተግባር በህግ አስፈፃሚው (executive branch) ተፅዕኖ ሥር ሲወድቅ በሥርዓተ ማህበረሰብ ላይ የሚያስከትለው ጉዳት ከፍተኛ ነው። በእኛ አገር ደግሞ በተለመደ አገላለፅ ተፅዕኖ (influence) ከምንለው በላይ በገዥው ፓርቲና በሚቆጣጠረው የመንግሥት አካል (ህግ አስፈፃሚው/ጠቅላይ ሚንስትሩና ካቢኔው )ቁጥጥር ሥር የወደቀ በመሆኑ በአገርና በህዝብ ላይ እያስከተለ ያለው የመከራና የውርደት ፅዋ ሞልቶ ከፈሰሰ ወራት ሳይሆን ዓመታት ተቆጠሩ ። እንግዲህ እንዲህ ዓይነቱን የመንግሥት ሥርዓት ነው ዘረኛና አምባገነን ገዥዎቻችን "በሙሉ ነፃነት የሚሠራው የፍትህ ሥርዓታችን"በማለት ያለሃፍረት የሚሰብኩን።

የህወሃት/ኢህአዴግ የፍርድ ቤትና የፍትህ ሥርዓት (judicial system) ተብየውን ባህሪና ተግባር በጥያቄ መልክ እንደሚከተለው ላቅርበውና በመሬት ላይ ከሆነውና እየሆነ ካለው መሪር ዕውነታ ጋር እያመሳከረ መልስ ይሰጥበት ዘንድ የአገርና የወገን መከራና ውርደት ከማሳሰብ አልፎ ህመሙ በብርቱ ይሰማኛል ለሚል የአገሬ ሰው እተወዋለሁ።

•በዕውቀት ብቃትና በሙያ ሥነ ምግባር ልዕልና ሳይሆን በአብዮታዊ ዴሞክራሲ (በገዥዎች ፍላጎትና አመለካከት) አፍቃሪነትና ታማኝነት መሠረት የሚመለመልና የሚሾም አቃቤ ህግና ዳኛ እንደ ጥሩ መደበኛ አሠራር በሚታይበት አገር ፍትህን (justice) ያህል ክቡር ነገር እንዴት መጠበቅ ይቻላል?

•ገዥው ፓርቲ እንኳንስ በቀጥታ የሚቆጣጠረውን የመንግሥት አካል ይቅርና ከሰፈር የመረዳጃ ማህበር ጀምሮ አገር አቀፍ የሙያን ፣ የሠራተኛ ማህበራትንና እና የሃይማኖት ተቋማትን በአንድ ወይም በሌላ መንገድ በተፅዕኖው ሥር ለማድረግ የማያቋርጥ ፣ ግልፅና ስውር ዘመቻ በሚያደረግበት አገር ፍትህ ሞቶ ቢቀበር ምን ያስገርማል ?

•የገዥውን ፓርቲና የሚቆጣጠረውን መንግሥት ባለሥልጣናት ፍላጎትና አካሄድ እየተከተለ እና ተፈብርኮ የሚሰጠውን የውንጀላ ክስ እያቀነባበረ ክስ የሚመሠርትና መብትን ከመጠየቅ ውጭ ሌላ ሃሳብና ዓላማ የሌላቸውን ዜጎች እስከሞት በሚደርስ ቅጣት ካልተቀጡልኝ ብሎ የሚሟገት አቃቤ ህግን በጉያው አቅፎ ከያዘ የመንግሥት ሥርዓት ትክክለኛውን የህግና የፍትህ ሂደት (due process of law) እንዴት እንጠብቅ?

•ለይምሰል ችሎት እየተቀመጠ የአቃቤ ህጉን የፍብረካ ወንጀል ድርሰት ተቀብሎ በንፁሃን ዜጎች ላይ እጅግ ከባድ ቅጣት (ፍርድ) በመወሰን ዕውነትን (truth) ጨምሮ የሚያጎሳቁልና የሚገድል ዳኝነት በተስፋፋበት የመንግሥት ሥርዓት ውስጥ ከመከራና ከውርደት ውጭ ሌላ ምን እንጠብቃለን?

•ጥፋተኛ አይደለምና/አይደለችምና ከዚህ ቀንና ሰዓት ጀምሮ ከሥር ነፃ ይሁን /ትሁን የምትለዋንና አልፎ አልፎ ስትከሰት እንደ ብርቅየ የምትቆጠረዋን የዳኛ ትዕዛዝ ፖሊስ ወይም የወህኒ ቤት (ማረሚያ ብሎ መጥራት የሰቆቃ ሰለባ በሆኑ ንፁሃን ዜጎች መቀለድ ነው) አዛዦች የፖለቲካ ልዩ ትዕዛዝ እስኪያገኙ ውድቅ በሚያደርጉበት የመንግሥት ሥርዓት ውስጥ የፍትህን ክቡር ዋጋ በዕውን ማየት ቀርቶ እንዴት ማሰብ ይቻላል ?

•ንፁሃን ዜጎች በየማጎሪያ ቤቱ የሚደርስባቸውን ኢሰብአዊ (አካላዊና ሥነ ልቦናዊ) አያያዝ "ለክቡር ፍርድ ቤቱ" ሲያስረዱና አቤት ሲሉ 'ክቡራን ዳኞች' "ጉዳዩ ተጣርቶ አስፈላጊው ይፈፀማል" ከማለት ያለፈ ህጋዊ እርምጃ

የመወሰዱ ነገር ጨርሶ ጉዳያቸው አይደለም ። የፖሊስ ባለስልጣኑ ከህግ በላይ የሆነውን ገዥ ቡድን ትዕዛዝ እንጅ የፍርድ ቤት ትዕዛዝ ግድ እንደማይለው እያወቁ ለማስመሰል ያህል "ከዛሬ ጀምሮ ተገቢው አያያዝ ይደረግላቸው" ሲሉ ቢያንስ የሞራል ውደቀት አይሰማቸም። ታዲያ ገዥዎቻችን እንዲህ ዓይነቱን የፍትህ ውደቀት ስኬት ነው ሲሉን እስከየትና እንዴት እንታገሳቸው?

•ገዥው ቡድን ድምፄ ይከበር ብሎ የጮኸውን ህዝብ አዋክቦና አሸብሮ ፣ እምቢ ለመብቴ በማለት የታገሉትን ዜጎች ደግሞ በማሰር ፣ በማሰቃየትና በመግደል እጅ በማውጣት የሰቆቃ አዋጁንና እርምጃውን የሚያፀድቅለትን ፓርላማ መቶ ፐርሰንት የመቆጣጠሩ ነገር ከአስቀያሚ የፖለቲካ ምዕራፎቻችን አንዱ ነው ። ከሁሉም በላይ በእጅጉ ልብ የሚሰብረው የፍትህ አካል ተብየው ለዚህ እጅግ አስከፊ የፖለቲካ ሥርዓት የህግ ሽፋን መስጠት ብቻ ሳይሆን ገዥዎች እየፈበረኩ የሚሰጡትን የክስ ድርሰት እያነበበ ለነፃነት ፣ ለሰበአዊና ዴሞክራሲያዊ ሙብት በጮሁ ንፁሃን ዜጎች ላይ ከባድ የፍርድ በትሩን እያሳረፈ መከራና ውርደትን የማራዘሙ ታሪክ ነው። ታዲያ ይህን የሰቆቃ ሥርዓት መሠረታዊ በሆነ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ለመተካት የመከራውና የውርደቱ መጠንና ደረጃው እስከምን ድረስ መሆን አለበት ? ፅዋው ሞልቶ ከፈሰስ አልቆየም እንዴ ?

•"ከቡራን ዳኞች" በብዙ ሽዎች በሚቆጠሩ ንፁሃን ዜጎች ላይ የግፍ ፍርድ እየፈረዱ ለምንና እንዴት ተብለው ሲጠየቁ በግፍ የሚፈረድባቸው ዜጎች የሚያሳድጓቸው ልጆችና የሚያስተዳድሯቸው ቤተሰቦች የሌላቸው ይመስል "ተውን ልጆቻችን እናሳድግበት" በሚሉባት አገር በየት በኩልና እንዴትስ ነው የህግን የበላይነትን የምንጠብቀው?

የተዘፈቅንበት ሁለንተናዊ ውድቀታችን እጅግ የከፋ በመሆኑ መልስ የሚሹ ጥያቄዎቻችን ብዛትና ፈታኝነትም የዚያኑ ያህል ነው ። በቅንነትና በአገራዊ ጀግንነት (genuinely and with a real sense of national patriotism) ከተዘጋጀን ግን መልሱ ቀላል ባይሆንም የማንመልሰው ግን በፍፁም አይደለም ። እንደሰውና እንደ ዜጋ ነፃነት ፣ የህግ የበላይነት (ፍትህ) ፣ ሰብአዊ ክብር ፣ እኩልነት ፣ አብሮነት ፣ ዕውነተኛ ሰላም እና የጋራ ብልፅግና በሰፈነባት አገር መኖር ካለብን ትግሉም የኛው ፣ በኛውና ለኛው ነውና እስከአሁንም ትውልድን እየገደለ፣ እያስገደለና እያገዳደለ ያለውን ሥርዓት በመሠረታዊ ዴሞክራሲያዊ ትግል የማስወገዱን ጥያቄ ለነገ የማለቱ አባዜ ማብቃት አለበት ። ከኢትዮጵያ ህዝብ መሠረታዊ ፍላግትና ጥቅም ጋር ጨርሶ የማሄድ (የማይገናኝ) የግል ወይም የቡድን ፍላጎትን በብሔር/ብሔረሰብ/ጎሳ ፍላጎት ስም እየቀባባን እኔ እበልጣለሁ ወይም እኛ እንበልጣለን የሚለውን የፖለቲካ አስተሳሰብ ለመለወጥና በአብሮነትና በመከባበር የጋራ ዕጣ ፈንታችን እኛው ካላበጀነው የእራሳችን ጠላት እራሳችን መሆናችን ልብ እንበል ። ወይም የቤተ መንግሥት ፖለቲከኞች (ገዦቻችን) ብዙ ጥሩ ነገር የመሥራታቸውን ያህል የሠሩትን ስህተት በትምህርትነቱ ሳይሆን ዛሬ መውጫ ማበጀት አቅቶን ከምንዳክርበት የፖለቲካ ዕውነት ጋር እያመነዠክን የትምና ወዴትም አንደርስምና ከምር በቃ! እንበል። ።

2.በዚህ ገዥዎቻችን ሲያመቻቸው ማታለያ ሲጨንቃቸው ደግሞ መቅጫና መቀጣጫ እያደረጉ በሚጠቀሙበት ህገ መንግሥት ውስጥ 15 የሰብአዊ መብቶችን እና 16 የዴሞክራሲያዊ መብቶችን በድምሩ 31 አንቀፆችን እናገኛለን። እነዚህን አንቀፆች በጥሞና አንብበንና የተሸከሙትን ግዙፍና ጥልቅ ትርጉም ተረድተን ሩብ ምዕተ ዓመት ከዘለቅንበትና እስከአሁንም ከምንገኝበት እጅግ አስከፊ ዕውነታ( horrible reality) ጋር ለማመሳከር ስንሞክር የሚሰማንን መሪር ስሜት ቃላት በበቂ ሁኔታ የሚገልፁልን አይመስለኝም ። ለዚህ የምርምር ወይም የጥናት ማስረጃ እንዲቀርብለት የሚጠይቅ ካለ ወይ የዚያው ብልሹና ወንጀለኛ ሥርዓት ቀጥተኛ ተጠቃሚ ነው ፣ ወይም በአንድ ወይም በሌላ መልክ የጥቅም ተካፋይ ነው ፣ ያለዚያ ደግሞ በአገር ውስጥም ሆነ በውጭው ዓለም ቁሳዊ ፍላጎቱ እስከተሟላ ድረስ የደመ ነፍስ አጋሰስነት የተጠናወተው መሆን አለበት። ምክንያቱም የአገራችን ሥርዓተ ማህበረሰብ (ፖለቲካዊ፣ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና ሞራላዊ) ውድቀትን የኢትዮጵያ ህዝብ ሌሎች ነግረውት የሚሰማዉና ጽፈውለት የሚያነበው ሳይሆን ድፍን ሩብ ምዕተ ዓመት እየኖረው ያለው የቀን በቀን የህይወቱ ገጠመኝ ነወና ።

3.ይህ የህጎች ሁሉ መነሻና የበላይ የሆነ ህግ ዴሞክራሲያዊ ወይም ኢ-ዴሞክራሲያ መሆኑን ለመረዳት መርሆዎችንና ድንጋጌዎችን የያዘ ሰነድ (constitution) ከመሆን አልፎ በመሬት ላይ (በተግባር) የአገርና የሕዝብ ደህነነትና ጥቅም ዋስትናነቱን መረዳትና ማረጋገጥን ግድ ይላል። በሌላ አገላለፅ ህገ መንግሥት (constitution) ከሰነድነቱ አልፎ ህገ መንግሥታዊነትን (constitutionalism ን) አረጋግጧል ወይ? ሥልጣን ላይ ያለውን ግለሰብ ወይም ቡድን ወይም አካል የሥልጣን አይነትና መጠን "ማንም ከህግ በላይአይደለም" በሚለው መሠረታዊ መርህ መሠረት ገደብ ጥሎበታል ወይስ በአገርና በህዝብ ጥቅምና ደህንነት ሽፋን የገደብ የለሽ ሥልጣንና ምዝበራ ማስፈፀሚያ ሆኗል ? ህገ መንግሥት የገደብ የለሽ የሥልጣን ብልግና ሽፋን የመሆኑን ወይም ያለመሆኑን ውጤት በዕለት ዕለት ሁለንተናዊ አኗኗራችን ሂደት ውስጥ ከማየት አልፈን ከምር በማስተዋልና በመረዳት ለምንና እንዴት ብለን እንጠይቃለን ወይስ የገዥዎቻችን ጉዳይ ነው በሚል እራሳችን አሳልፈን እንሰጣለን? ብሎ የመጠየቅና የማረጋገጥ አስፈላጊነት ፍፁም ነው። የዴሞክራሲያዊ

ሥርዓት ለውጥን ፣ ግንባታንና ዘላቂነትን ከምር የምንሻ ከሆነ ።

ምንም እንኳ በረጅሙ የፖለቲካ ታሪካችን ሂደት ዴሞክራሲያዊ ቀርቶ የዴሞክራሲ ሽታ ያለው ህገ መንግሥታዊ ሥርዓት ኖሮን ባናውቅም ሶስት አሥርተ ዓመታት ሊደፍን የተቃረበዉና አሁንም ለመቀጠል የመጨቆኛ (የመደፍጠጫ) መሣሪያውን ( state machinery) በህዝብ ላይ ከማዝመት ወደ ኋላ ያላለው የህወሃት/ኢህአዴግ አገዛዝ "ዴሞክራሲያዊ" በሚለው ህገ መንግሥቱ ሽፋን አገርና ህዝብን እጅግ አደገኛ ቀውስ (crisis) ውስጥ እንደዘፈቀ ለመረዳት "ካላሳመናችሁኝ አላምንም" የሚል ካለ አንድም ከቀውሱ ፈጣሪዎች ጋር በመተሻሸት በሚያገኘው ጠቀም ያለም ይሁን ፍርፋሪ ጥቅም ሰብዕናውን ጨርሶ ያቆሸሸ ነው ፥ ያለዚያም "ባይገባኝ ምን አገባኝ" የሚል ከደመነፍስ እንስሳ በታች የወረደ መሆን አለበት።

ይህን ስል አንድ ሥርዓት ማህበረሰብ (ዴሞክራሲያዊም ቢሆን) በሰው ሠራሽ ወይም ከሰው ቁጥጥር ውጭ በሆነ ምክንያት ቀውስ (crisis) ፈፅሞ አያጋጥመውም ለማለት አይደለም ። ዕውነተኛ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት በባህሪውና ከባህሪው የሚመነጩና የማይናወጡ መርሆዎቹን ፣ ህጎቹንና የአፈፃፀም ስልቶቹን ተጠቅሞ ከተቻለ ለቀውስ ምክንያት ሊሆኑ ለሚችሉ ጉዳዮች አስቀድሞ መፍትሄ በመስጠት ቀውስን ያስቀራል ፣ ይህ ባይሳካ እንኳ የሚከሰተውን ቀውስ በፍጥነትና በብቃት በመቆጣጠር አገርና ህዝብን ከገቡበት ፈተና ማዉጣት ብቻ ሳይሆን ይበልጥ ጠንክሮ ለመውጣት ያስችላል ለማለት እንጅ። እኛንም እንደ አገርና እንደህዝብ በእጅጉ እየተፈታተነን ያለው ፈተና ይኸው ነው።

በአንድ ማህበረሰብ ውስጥ የሚፈጠር ችግር ከችግርነት አልፎ ቀውስ በመሆን አላስፈላጊና ከባድ ጉዳት የሚያስከትለው በአንድ በኩል ሥልጣን ላይ የተቀመጡ ግለሰቦች ወይም ቡድኖች የህዝብ ጥቅምና ደህንነት ግድ የሚላቸው ሳይሆኑ ገደብ የለሽ የሥልጣን ብልግናቸውን በመጠቀም የራሳቸውን ፍላጎትና ጥቅም ለማርካት የወሰኑ ሲሆኑ ፣ እና በሌላ በኩል ደግሞ ሥርዓቱን ለመለወጥ እንፈልጋለን ወይም እንታገላለን በሚሉ ግለሰቦች ፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች ፣ የሰብአዊ መብት አይጣስ በሚሉ ድርጅቶች ወይም ግለሰቦች ፣ ሙያችን ይከበር በሚሉ ባለሙያዎች ፣ የዕምነት ነፃነት ይከበር በሚሉ የሃይማኖት ተቋሞች መካከል ከተመሳሳይ ምሬትና የማይጨበጥ የተስፈኝነት ዲስኩር (rhetoric) አልፎ የሚሄድ አገራዊና ወገናዊ የጋራ ራዕይና ተግባር ለመፍጠር ሳይችሉ (ሳይፈልጉ) ሲቀሩ ነው። ይህን የእራሳችንን መሪር ሃቅ በድፍረት ተጋፍጠን ትክክለኛውንና እንደ ሰው ሰው ሆነን ፣ እንደ ዜጋ ኮርተንና ተከብረን የምንኖርበትን ሥርዓት ማህበረሰብ በአብሮነት ትግላችን ዕውን ለማድረግ የሚያስገድደን ከአሁኑ የበለጠ መከራና ውርደት የምንጠብቅ ካለን በቅድሚያ እራሳችን ከዚህ ዓይነት ከፉ አባዜ (illusion) ነፃ መውጣት አለብን። ።

4.የአንድ አገር ህገ መንግሥት በተለይ ደግሞ ዴሞክራሲያዊ አንድነትንና በዚሁ የአንድነት ጥረት የሚገኝ የጋራ ብልፅግና ፣ዘላቂ ሰላምና ሁለንተናዊ ደህንነት ተልኮው (ግቡ) የሆነ በመግቢያው (preamble) ላይ በማንና ለምን የህጎች ሁሉ የበላይ እደሆነ የሚያውጁት ቃላት እጅግ ግዙፍና ጥልቅ መልክት የተሸከሙ ናቸው። አዎ! "እኛ የዚህ አገር ህዝቦች (We the People of ….)" ብለው የሚያውጁልንን እነዚህን ቃላት በትክክለኛው ትርጉማቸው ወደ ተግባር ለሚተረጉማቸው የህዝብን ሉአላዊ ሥልጣን ምንነት ከምንም በፊት አስቀድመው የሚያውጁ ናቸው። እዚህ ላይ "እኛ ህዝቦች" ስንል "We the peole" የሚለውን የወል ስም (collective noun) እንደ አንድ አገር ህዝብ መግለፃችን እንጅ የልዩነትና የጥላጫ ብዙሃነትን ህገ መንግሥታዊ አድርገው የመከራና የውርደት ህይወት ተጠቂዎች ካደረጉን ገዥዎቻችን መሰሪና መርዘኛ የፖለቲካ ጨዋታ ጋር ጨርሶ ግንኙነት የለውም። የከፉ መንፈስ (አስተሳሰብ) እና የኢሰብአዊነት ባህሪ የተጠናወታቸው ገዥዎቻችን ሲፈልጉ በሚያታልሉበት ሲያሻቸው ደግሞ እየጠቀሱና እያጣቀሱ በሚያስሩበት ፣ በሚያሰቃዩበትና በሚገድሉበት የህገ መንግሥታቸው መግቢያ ላይ ያወጁሉን የልኡአላዊ ሥልጣን ምንጭ የኢትዮጵያ ህዝብ ( We the people of Ethiopia) መሆኑን ሳይሆን "እኛ የብሄሮች ፣ ብሄረሰቦችና ህዝቦች (We the nations, nationalities and peoples)" ብለው ነው።እርግጥ ነው ቀደም ባለው ታሪካችን አገራዊ ነፃነታችን ((territorial integrity and sovereignity) በደምና አጥንት መሥዋዕትነት ከማስከበር አልፎ ለእኛው ክፍለ ዓለም (አፍሪካ) ብቻ ሳይሆን በመላው ዓለም በቅኝ አገዛዝ ሥር ይማቅቁ ለነበሩ የዓለም ህዝቦች ሁሉ አንፀባራቂ አርአያ የመሆኑን ሃቅ የህወሃት/ኢህአዴግ የጥላቻና የማጋጨት ፖለቲካ ከቶውንም አይለውጠውም። የአንድ አገር ህዝብነቱ ወደ የመጣበት ብሔረሰብ/ጎሳና የመኖሪያ አካባቢ ፣ የሚናገረው ቋንቋ ፣ ባህልና ወግ ወርዶ የአያቶቹና የቅድመ አያቶቹ ደም ተቀላቅሎና አጥንትም ተነባብሮ የታተመበትን ኢትዮጵያዊነትን ከዚህ ትውልድ ፖለቲካዊ፣ ሞራላዊና ሥነ ልቦናዊ ማንነት ጋር እያጋጩ ሥልጣንን የማስቀጠልና ኢኮኖሚያዊ ምዝበራን የማጠናከር አባዜ በእጅጉ ሊያሳስበን ይገባል።

የኢትዮጵያ ህዝብ እንደማነኛውም በልዩነት ውስጥ አብሮ እንደሚኖር ህዝብ በኢትዮጵያዊ ማንነቱ ለዘመናት አብሮ ያልዘለቀ ይመስል የወል ሉአላዊነቱን (collective soverreigny ) እኛ ብሄሮች ፣ብሄረሰቦች እና ህዝቦች በሚል መንዝረውና በህገ መንግሥት ደንግገው እኛና እነዚያ/እነሱ እያለ እርስ በርሱ ሲፈራረጅና ሲናቆር እነሱ (ገዥዎቻችን) ይኸዉና ቀጥቅጠውና እያስራቡ ከገዙን ከሩብ ምዕተ ዓመት በላይ አስቆጠሩ። የኢትዮጵያ ህዝብ የዘመናት ችግር የዕውነተኛ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት እጦት እንጅ እራሱን በትንንሽ የመንደር መንግሥታት ከፋፍሎና እርስ በእርሱ ተበላልቶ

የመጨራረስ ጥያቄ ያቀረበ ይመስል “ከፈለግህ የመገነጣጠል መብትህ የሚስትና የባል የመጋባትና የመፋታትን ያህል ቀላል ነው “ ብለው የህገ መንግሥታቸውን “የድል ገድል አበሰሩለት” ። ይህን ገድል ባበሠሩበት ህገ መንግሥት ስም ግን ብሄር/ብሄረሰብ ሳይለዩ ነፃነት ፣ ፍትህ ፣ እኩልነት ፣ ሰብአዊ ክብርና የጋራ ብልፅግና የጠየቀን ሁሉ አይቀጡ ቅጣት እየቀጡና የአገሩን አንጡራ ሃቡት እየዘረፉ ሩብ ምዕተ ዓመት ዘለቁ።
በጎሳ ማንነት ላይ የሚመሠረት የፖለቲካ ሥርዓት ብዙ ቁጥርም (majority) ሆነ አናሳ ቁጥር (minority) ካለው ወገን ይምጣ ከዕውነተኛ ዴሞክራሲዊ ሥርዓት ጋር የሚገጥም ተፈጥሮና ባህሪ ጨርሶ የለውም። እንደ ህወሃት በቁጥር አናሳ (minority) የሆነውን ብሔረሰብ/ጎሳ መሠረት ያደረገ ሲሆን ደግሞ በአገርና በህዝብ ላይ የሚያስከትለው መከራና አደጋ እጅግ የከፋ ነው። ለሩብ ምዕተ ዓመት የመጣንበትና አሁን ያለንበት መሪር ዕውነት የሚነግረንም ይህንኑ ነው ። እናም ከዚህ በኋላ ከታሪክ የማይማሩና ከጥፋት የማይመለሱ የአገዛዝ ቡድኖችን እብደት ከመሠረታዊና ዴሞክሩሲያዊ የሥርዓት ለውጥ ባነሰ የትግል ስትራቴጅ ፣ ፕሮግራምና እቅድ ዕውን ለማድረግ ቀርቶ ማሰብም ወይ ስሜት የማይሰጥ የፖለቲካ ቂልነት/ድንቁርና ነው ፣ ወይ የከረፋ አድርባይነት ነው ፣ ወይም መከራና ዉርደትን ተቀብሎ የመኖር(ኑሮ ከሆነ) ተሸናፊነት ነው ።

5.በሥርዓት ለውጥ አስፈላጊነት ስብከታችን ( rhetoricaly) እየተስማማን ወደ ተግባር ስንገባ ግን አለመስማማትና አለመተባበር ብቻ ሳይሆን እየተጠላለፍን ለዘመናት ከመዝለቃችን አባዜ ለመዉጣት የሚጠይቀን ሃላፊነት እጅግ ግዙፍና ፈታኝ ነው። ይህ ፈተናችን ከህዝብ የፖለቲካ ንቃተ ህሊና እና የአኗኗር ድህነት ጋር ተጨምሮ ይኸውና ገዥዎቻችን ዴሞክራሲያዊ በሚሉት ሰነድ (ህገ መንግሥት) ሽፋንነት እያታለሉ መቀጠሉ አላዋጣቸው ሲል “ፀረ ሽብር” የሚል አዋጅ አወጁና ያንኑ የውሸት (fake) የህጎች የበላይ ህግ እየጠቀሱ መቅጫና መቀጣጫ አደረጉት። የአገርና የወገን ውርደትና መከራ ይብቃ ብለው በዜግነታቸው ፣በየሙያ ተቋሞቻቸው ፣ በየሲቪክ ማህበሮቻቹውና በየፖለቲካ ድርጅቶቻቸው በጮሁ ፣ ህዝብን ባሳወቁ ፣ ባደራጁ እና በአገሩ ተከብሮና ኮርቶ ይኖር ዘንድ ባታገሉ አያሌ ንፁሃን ዜጎች “አሸባሪዎች” ተብለው መዋከባቸው ፣ የቁም ስቃይ ሰለባ መሆናቸው ፣ በየማጎሪያ ማዕከሉና በየወህኒ ቤቱ ተወርውረው የግፍ ዓይነት መፈተኛ መሆናቸው፣ የደረሱበት ጠፍቶ ለቤተሰብና ለወዳጅ ዘመድ ጊዜ የማይፈታው የልብ ስብራት መሆናቸው ፣ እና በገዥዎች ቀጭን ትዕዛዝ የማይተካ ህይወታቸውን የማጣታቸው ጉዳይ ለቤተሰብና ለወዳጅ ዘመድ የዕድሜ ልክ ሃዘን የመሆናቸው ነገር በአብሮነት የሚበጀንን የሥርዓት ለውጥ ዕውን ለማድረግ ባለመቻላችን መሆኑን ከምር ካሰብነው ልብ ይሰብራል ። እንደማነኛውም ባለታሪክ ህዝብና አገር ከነችግራችንም ቢሆን የአኩሪ ታሪክ ባለቤት ነን ለምንል ደግሞ ህመሙ በእጅጉ ከባድ ነው። ለዚህ ነው ከመሠረታዊ ዴሞክራሲያዊ የሥርዓት ለውጥ ያነሰ የፖለቲካ ትግል አገርና ህዝብ አሁን ለሚገኙበት እጅግ አሳሳቢ ሁኔታ ጨርሶ አይመጥንም ማለት ትክክል የሚሆነው።

6.ከላይ በአጭሩ እንደገለፅኩት በዚሁ “ዴሞክራሲያዊ ህገ መንግሥታችን” በሚሉት የአገዛዝ ሰነዳቸው ውስጥ ባሰፈሯቸው የሰብአዊና ዴሞክራሲዊ መብቶች ሥር የመናገርና የመፃፍ ወይም ሃሳብን የመግለፅ ነፃነት ተረጋግጧል የሚሉ ወርቃማ አንቀፆች ተዘርዝረዋል ። በዚህም መሠረት አገርና ህዝብ ለአያሌ ዘመናት የዘለቁበት መብት አልባ የፖለቲካ ታሪክ እና ከሩብ ምዕተ ዓመት ወዲህ ደግሞ የሄዱበት የውርደትና የመከራ ቁልቁለት ያበቃ ዘንድ ጥረት ባደረጉ አያሌ አንጋፋና ወጣት የሚዲያ ባለሙያዎች ላይ ወይም በእራሱ በሙያው ላይ የአገርንና የህዝብን ደህንነት ለማስጠበቅ በሚል ሌላ የማሸበሪያ አዋጅ (“የፕሬስ አዋጅ”)አወጁ። የሃሰት ማስረጃና ምስክር አዘጋጅተው ስለፍትህ ተምሮ ተመልሶ ፍትህን በገደለ ካድሬ ወይም ስለፍትህ ተምሮ ፍትህን በሆዱ በለወጠ አቃቤ ህግ እና ዳኛ የግፍ ፍርድ እያስፈረዱ ወደ ሰቆቃ መፈፀሚያ ማዕከሎቻቸውና ወህኒ ቤቶታቸው ወረወሩ ፣ አንገላቱ ፣ ሰቆቃ ፈፀሙ ፣ከአገር አሳደዱ ፣ የቤተሰብና ወዳጅ ዘመድን ህይወት እጅግ መሪር አደረጉ ። እናም ለዚህ ነው የሥርዓት ለውጥ ስንል ይህን ዓይነት የግፍ ፣የመከራና የውርደት የፖለቲካ ሥርዓት ከመሠረቱ ነቅሎ በአዲስና ዕውነተኛ ሥርዓት የመተካት አስፈላጊነት ፈፅሞ ለድርድር የሚቀርብ አይደለም ማለታችን ዕውነትና ትክክል የሚሆነው። ይህን ዕውን ለማድረግ ደግሞ በቁርጥ ቀን የኢትዮጵያ ልጆች መሪነትና አስተባባሪነት እና በህዝብ ንቁና የማይበገር ተሳትፎ እንጅ ከቶውንም ለአገርና ለወገን ሲሉ ከስህተት የመማር የሞራልም ሆነ የፖለቲካ ሰብእናቸው ካልፈቀደላቸው የአገዛዝ ቡድኖች ጠይቀን የምናገኘው አለመሆኑን ከምር ማመንን ግድ ይላል።

7.በትክክልና በአግባቡ ለሚጠቀምበት የመድብለ ፓርቲ ፖለቲካ ሥርዓት(multi–party political system) ህዝባዊና ዴሞክራሲያዊ ሥርዓተ ማህበረሰብ ከሚገለፅባቸው ዋና ዋና ሁኔታዎች መካከል አንዱ ነው። መሠረታዊ ምክንያቱ ደግሞ የፓርቲ ቁጥር መብዛት በራሱ ጠቃሚ ሆኖ ሳይሆን፡- ሀ) ዜጎች ተደራጅተው የሚወክሉትን

አስተሳሰብና ይገባናል የሚሉትን ፍላጎትና ጥቅም ማራመዳቸው(ማስጠበቃቸው) የማይገሰስ ዴሞክራሲያዊ መብታቸው ስለሆነ ለ) ዜጎች እንደዜግነታቸም ሆነ እንደ ሰብአዊ ፍጡርነታቸው የየራሳቸው ዕውነትን የሚያዩበት እይታና የሚረዱበት መንገድ ወይም አካሄድ ስለአላቸው ይህኑ ሙብት (መደራጀትን) መከልከል ወይም ማፈን ዕውነትን እራሱን ማፈን በመሆኑና በማህበረሰቡ ላይ የሚያስከትለው ጉዳት ከባድ ስለሚሆን ሐ)ከዚህ መሠረታዊ ሙብት ያለገደብ ተግባራዊ መሆን ተጠቃሚ የሚሆነውን ህዝብ መሠረታዊ ዴሞክራሲዊ ሙብት መደፍጠጥ ስለሌለበት መ) እንደ አገርና እንደህዝብ ዕድገትና ብልፅግናን ለማረጋገጥ እንዲህ ዓይነት መሠረታዊ የመደራጀት መብቶች በነፅነት ከማሰብና ሃሳብን ከመግለፅ ጋር ተጣምረው የሚኖራቸው አስተዋፅኦን ማፈን ይቅርና ማቃለል ፈፅሞ የጤናማ ማህበረሰብ ባህሪና ፍላጎት ሊሆን ስለማይችል ነው። ።

ህወሃት/ኢህአዴግ ሥልጣኑን ካደላደለ በኋላ የህዝብን ልብ ለመግዛትና ለዓለም መንግሥታት በተለይ ለምዕራባዊን "አጋሮቹ" መስሎ ለመታየት የከፈተውን በር በመጠቀም ደሃ አገር ሊሸከመው ከሚችለው በላይ የፖለቲካ ድርጅት ነን የሚሉ እንደ አሸን ቢፈሉም አንፃራዊ በሆነ መልኩ የህዝብን ቀልብና ድጋፍ የሳቡት ግን እጅግ በጣት የሚቆጠሩ ነበሩ ። ምንም እንኳ የነበራቸው ሚና በአብዛኛው ስለገዥው ፖርቲ አምባገነናዊነት ንግግር ከማድረግ ወይም ከማማረር ያለፈ ባይሆንም የተወሰነ የወንበር ቁጥር አግኝተው ፖርላማ ተሰይመው የነበሩ ተቀዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎች እንደነበሩም የሚታወስ ነው።
ህወሃት/ኢህአዴግ ግን ተፎካካሪ የፖለቲካ ፓርቲዎች ገዝፈውና ደፍረው ፈተና ላይ እንዳይጥሉት ማሽማቀቁን ፣ ማዋከቡንና ሲፈልግም ወደ እሥር ቤቱቹ መወርወሩን አቁሞ አያውቅም ። ይህ ተፈጥሮውና ባህሪው ጨርሶ ወደ ለየለት እብደት የተሸጋገረው የ 1997 ዓ.ምቱን የምርጫ ሂደትና ውጤት ተከትሎ ነበር ።
ያንን ትልቅ ተስፋ ያጫረውን ፖለቲካዊ ሁኔታ ተጠቅመው ንቁ ተሳትፎ ያደረጉ ድርጅቶች በተለይም የቅንጅትአመራርና አባላት የህወሃት/ኢህአዴግ የፖለቲካ ጨዋታ (ድራማ) መጋረጃ እንዲጋለጥ ብቻ ሳይሆን እንዲቀደድ ማድረጋቸውን በአድናቆት ፣ አሳዛኝ ውድቀታቸውን ደግሞ በፀፀትና ቁጭት የምናስታውሰው የፖለቲካ ታሪካችን አንድ ጉልህ አካል ነው።
የፖለቲካ ዙፋናቸውን በጎሳ ከፋፍሎና አጋጭቶ የመግዛት መሠረት ላይ የተከሉ አምባገነን ቡድኖች ተፈጥሯቸውና ባህሪያቸው የማይፈቅድላቸው በመሆኑ "ዕውነት አለን ፣ እንደማመጥና በዕውነት እንዳኝ" ብለው የጮሁ ዜጎች በቀጥታ ከቤተ መንግሥት በተሰጠ ትዕዛዝ ተዋከቡ ፣ ተደበደቡ ፣ በየማጎሪያ ማዕከሉ ተጋዙ ፣ በሃሰት ተወንጅለው የሃሰት ፍርድ ሰለባዎች ሆኑ ፣ ተገደሉ ።
እንኳን በተግባር የተንቀሳቀሰ ቀርቶ የሰላምና ፍቅር ምልክት ያሳየም ቆራጭ ሰይፍ እንደሚያጋጥመው ያልተፃፈ አዋጅ ታወጀበት። አሁን የሌሉትና የያኔው "ታላቁና ፈላስፋው መሪ (the philosopher king)" አቶ መለስ ዜናዊ ለሰላማዊ የፖለቲካ ሥርዓት ለውጥ ፣ ለድምፄ ይከበር ፣ ለፍቅርና ለአብሮነት የተዘረጉትን ጣቶች (የቅንጅት አርማ) "ካልታጠፉ (ካልተሰበሰቡ) ይቆረጣሉ" ማለታቸውን ስናስታውስ የመድብለ ፖርቲ መሠረተ ሃሳብና መርህ በአገራችን እንዴት ተራ የአምባነኖች የፖለቲካ ቁማር እንደሆነ ግልፅና እጅግ መሪር ዕውነት መሆኑን እንረዳለን። የአገርና የወገን መከራና ውርደት ውርደታችን አይደለም የምንልና ከደመነፍስ እንስሳም በታች የወረድን ደካሞች ካልሆን በስተቀር ።
በዚያ "የአብዮታዊት ኢትዮጵያ" ዘመን የወታደራዊው ፖርቲ ሊቀመንበርና የአገሪቱ መሪ የነበሩት ኮሎኔል መንግሥቱ ኃይለማርያም በያኔው አብዮትና በአሁኑ መስቀል አደባባይ አብዛኛው ወዶ ሳይሆን ተገዶና ፈርቶ ቁጥሩ እጅግ ብዙ የሆነ ህዝብ በተገኘበት አጋጣሚ በደም ተምሳሌነት በፈሳሽ ቀይ ቀለም የተሞላ ጠርሙስ አስፋልት ላይ ከስክሰው "ደማቸውን እንደዚህ እናፈሰዋለን" ብለው የፎከሩትን ጭራቃዊ ዕብደት ከፋይል እያወጡ "እንዚያን እርኩሳን እኛን ግን ቅዱሳን" በሉን የሚሉን አቶ መለስና ጓዶቻቸው አዋከበው፣ አሰቃይተውና ገድለው የህዝብን ድምፅ መዝረፉ አልበቃቸው ብሎ ለምን? ብሎ የጠየቀውንና የሰላምና ፍቅር ምልክት ጣቶቹን ያሳየውን ህዝብ አርፈህ ባትቀመጥ እንቆራርጥልሃለን ሲሉትና ያሉትንም ሲያደርጉት ከመመስከር የባሰ የመከራና የውርደት መርዶ የለም። ። ጣት ብቻ ሳይሆን የሽዎችን ንፁሃን ሙሉ ህይወት በቀጭን ትዕዛዝ ሲያስቀጥፉ እያለቀስንና እየተላቀስን አየን ። ይህን እጅግ መሪር መከራና ወርደት ከእርሳቸው ሞት ጋር ወደ መቅበር እንዲወርድ ማድረግ ባለመቻላችን ይኸውና የእርሳቸው የሙት መንፈስ ሌጋሲ የዕብደት ሰይፍ የህዝብ የነፃነትና የፍትህ ጩኸት ባለበት ቦታና ጊዜ ሁሉ እየተምዘገዘገ ጭራቃዊ ተልኮውን በመፈፀም ላይ ይገኛል ።
አስራ ሁለት ዓመት ሙሉ (ከ 1997 ጀምሮ) ያው እብደት ሳያቋርጥ የሚያስከትለውን የመከራና የውርደት ቀንበር ሰባብሮ መውጣት አቅቶን ይኸውና አሁን ከደረስንበት ላይ መድረሳችን ልብ እንበል ። አዎን! በአሁኑ ወቅት ገዥ ቡድኖች ለማስመሰያነት ሲያስፈልጋቸው ከመሳቢያቸው እያወጡ ማጥቂያ ያደረጉትን ህገ መንግሥት አክብረን ሰላማዊ ትግል ብቻ እናደርጋለን የሚሉ ድርጅቶች ጠንካራ የሆነ አገራዊ ራዕይ ያላቸውን የአመራርና ተራ አባላትን በየእስር ቤቱ አስቀፍድደው እራሳቸውም በስም ካልሆነ በስተቀር ከምንገኝበት የአገራችን አደጋ አንፃር በተግባር የሉም ። መኖራቸው በዕውነት የሚዳሰስና የሚጨበጥ ቢሆን ኖሮ ምንኛ በታደልን። እራሳችንን ካላታለልን በስተቀር ዕውነቱ ግን እርሱ አይደለም ። ጠንክረው በመውጣት የሥርዓት ለውጥ ኃይሎች አካል

ይሆናሉ ወይስ ጥቂት ወንበሮችን ከገኘው ቡድን በስጦታ መልክ በማግኘት ባዶ ዲስኩር ለመደስኮርና የምሬት ፖለቲካ ለማጮህ ህይወት አልባውን ፓርላማ የቀላቀላሉ የሚለውን አብረን የምናየው ነው፡፡

8.በዴሞክራሲያዊ መብቶች ሥር ከተዘረዘሩት ጉዳዮች አንዱ ማንኛውም ሰው ማሳካት በሚፈልገው ተልዕኮና ዓላማ ዙሪያ የመደራጀት ወይም የመሰባሰብ መብቱ (freedpm of association) የተረጋገጠና የተከበረ ነው የሚል ነው፡፡ ይህ የዜጎችን/የሰዎችን ተፈጥሮና መሠረታዊ የሲቪል መብቶችን የማክበር ድንጋጌ ትርጉሙ ሰፊና ጥልቅ ነው ፡፡ በዚህ የመደራጀት መሠረታዊ መብት ተጠቅመው በሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች መስክ ጠቃሚ ተሳትፎ ከሚያደርጉ አካላት መካከል መንግሥታዊ ያልሆኑ (መያድ/NGOS) ይገኙበታል፡፡ ፡፡ በትምህርት ፣በሥልጠና ፣ከዓለም ዙሪያ የሚያካብቱትን ልምድ በማካፈል ፣ የቅድመ ምርጫ ሂደትን በመከታተል ፣ የምርጫ ክንውንንና የውጤት ቆጠራን በመታዘብ እና ትዝብታቸውን በተጨባጭነትና ሚዛናዊነት በማካፈል (በማቅረብ) የሚያደርጉት አስተዋፅኦ ከፍተኛ ነው ፡፡ በተለይ ህዝብን ማታለሉ አልሳካ ሲል በማዋከብ፣ በማሳደድ ፣ በማሰር ፣በመግደል ሥልጣንን ለማስጠበቅ እና ይህም አልሳካ ሲል የህዝብን ድምፅ በተቀናጀ መንገድ ዘርፎ ድል በሚታወጅበት እንደኛ ባለ አገር ውስጥ አስፈላጊነታቸው በእጅጉ የጎላ ነው ፡፡ በእኛ አገር ለሩብ ምዕተ ዓመት የሆነውና አሁንም እየሆነ ያለው ምን እንደሆነ እንኳን ለእኛው ለራሳችን ሰው መሆኑ ብቻ አሳስቦት በየዓለም ዙሪያው ሆኖ ለሚታዘብ ለማስረዳት ብዙም መድከምን የሚጠይቀን ጉዳይ አይደለም፡፡

ገዥዎቻችን አታሎ የመግዛት እና የሴረኝነት ፖለቲካቸው ለመንበረ ሥልጣናቸው ጊዜአዊ ዋስትና እንኳ ለመሆን እንደማይችል አምርረው ከተማሩባቸው አጋጣሚዎች ሁሉ የ 1997 ቱ የምርጫ ሂደትና ምርጫ ጉልህ ድረሻውን ይይዛል፡፡ ያን ዓይነት የህዝብ የሥርዓት ለውጥ ፈላጊነት ከምኞት አልፎ ድምፅን በመስጠት ብቻ ሳይሆን ድምፄን አላሰርቅም በሚል መስዋዕትነት እስከመክፈል የተሄደበትን ፖለቲካዊ ክስተት ከረዱት በርካታ ሁኔታዎች መካከል በዴሞክራሲ እና በሰብአዊ መብቶች ዙሪያ የተሰማሩ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ያደረጉት በጎ ተፅዕኖ እንደነበር የሚዘነጋ አይደለም፡፡

ይህ ሁናቴ በተለይ በአናሳ የጎሳ ፖለቲካ (minority ethnic politics) ቀመር ላይ የቆመውን የህወሃት ቡድን ከማናደድ አልፎ የፖለቲካ ዕብደቱን ጨመረበትና የህዝብን ድምፅ በተጠንቀቅ ያቆመውን የስቃይና የግድያ ኅይሉን አዝምቶ እና እራሱ ቆጣሪ ፣ ታዛቢ እና "የድሉን" አዋጅ ነጋሪ በመሆን "በእኔ ፍቅር የነደደ ህዝብ ያጎናፀፈኝን ድል የሚተናኮል/የምትተናኮል ካለ/ካለች እርሱን/እርሷን አያርገኝ" ብሎን እርፍ ፡፡

የህዝብን ድምፅ ቀምቶና እንዴት ብሎ የጠየቀን ህዝብ በጅምላ እሥርና በግድያ ፀጥ አሰኝቶ የድል አዋጁን ያወጀው ገዥው ቡድን የጥፋት እጁን መንንግሥታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች ላይ ለማሳረፍ የህግ ሽፋን ማዘጋጀት ነበረበት፡፡ እናም ከሁለት ዓመት የሴራ ጥናትና ምክክር በኋላ በ 2001 ዓ.ም "የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት" የተሰኘ አወጅ አወጀ፡፡ የአዋጁ ዕውነተኛ ተልዕኮውና ግቡ "ከፈለጋችሁ በተአምራዊው የልማትና ዕድገት ግስጋሲያችን ተንቀሳቀሱ ፥ ዴሞክራሲና ሰብአዊ መብት እና እገሌ መሌ የምትሉትን ግን ለእኛና እኛን ለሚመስለሉ ተውት" የሚል ነው፡፡ እናም ይህ ሶስተኛውና የራሳቸውን ህገ መንግሥት የደፈጠጠ አዋጅ መሆኑ ነው ፡፡ ህገ መንግሥታችን ናዳችሁብን ፣ እንደ ቆሻሻ የቅርጫት ወረቀት ቆጠራችሁብን ፣ እና ሌላም ሌላም ብለው የሚያላዝኑብን እንዲህ እራሳቸው በአዋጅና ያለአዋጅ ዋጋ ያሳጡትን ነገር ግን ለማጥቂያነት ከአቧራ አራግፈው የሚጠቀሙበትን ሰነድ ነው፡፡ ልብ ብለናል ?

እናም የሥርዓት ለውጥ ስንል ለሩብ ምዕተ ዓመት እንዲህ የመከራና የውርደት ማቅ ያከናነበንን የባለጌዎች ሥርዓት በቃ ብለን ዕውነተኛ ህዝባዊት ዴሞክሩሲያዊት ኢትዮጵያን እንመሥርትና እንገንባ ማለታችን ነው፡፡

9.የፖለቲካው ሥርዓት በጥቂት ጎሰኛ አምባገነኖችና በጥቅም ተጋሪዎቻቸው ቁጥጥር ሥር በዋለበት ሁኔታ ጤናማና እየበለፀገ የሚሄድ ይቅርና የህዝብን እጅግ መሠረታዊ ፍላጎቶች የሚያረጋግጥ የኢኮኖሚ (የምጣኔ ሃብት) ሥርዓትን መጠበቅ በየራሳችን የግል ወይም የቡድን ስግብግብ ፍላጎትና ጥቅም ህሊናችን ካልታወረ በስተቀር የእንተማመን ክርክር የሚያስፈልገው አይደለም፡፡ ገዥዎቻችን በዚህ ረገድ መጀመሪያ ዒላማ (target) ያደረጉት ዋናውን የምጣኔ ሃብት ምንጭ መሬትን ነው፡፡ የአገሬ ህዝብ ተወልዶ የሚያድግበትን ፣ ለቁም ነገር የሚበቃበትን ፣ የኑሮ ዋስትናውን ፣ የአገር ባለቤትነት ስሜት አውታሩን እና በመጨረሻም በክብር መቀበሪያ መሬቱን ህገ መንግሥታችን በሚሉት ሰነዳቸው "የአንተና የአንተ ብቻ ነው" ብለው ፃፉለትና በተግባር ግን የእነሱና የጥቅም ተጋሪዎቻቸው ብቻ መሆኑን ለዘመናት ከኖረበት ቦታውና ለም መሬቱ እያፈናቀሉ በገዛ አገሩ ለማኝ አድርገው አሳዩት ፡፡ ለእነሱና ለጥቅም ሸሪኮቻቸው ጉልበቱን በርካሽ ሸጦ ለማደር እንኳ የእነሱ ቆሻሻና ወንጀለኛ የፖለቲካ ጨዋታ አጃቢና "ገፅታ ገንቢ" ሲያደርጉት የሞራል ነውርነት ስሜት እንኳ ጨርሶ የላቸውም ፡፡

መሬትን በላዩም ሆነ በውስጡ ከያዘው ሃብት ጋር ከተቆጣጠሩ በኋላ በሚያስገርም ሁኔታ ዘመቻ ያደረጉት በፓርቲ ደረጃም ሆነ በግል ከትንሹ የኢኮኖሚ ዘርፍ እስከ ትልቁ የንግድና የኢንቨስትመንት ዘርፍ ኩባንያዎቻቸውን በውስጥና በውጭ ከሚገኙ የጥቅም

ተካፋይ ባለሃብቶች ጋር በማስተሳሰር የአገርን ሃብትና ንብረት ሙሉ በሙሉ በሚያሰኝ ደረጃ መቆጣጠር ነው ።
የዚህ ውጤት ደግሞ የቁጥር ጨዋታ (statistics and data) ፍለጋ የሚያስኬደን ሳይሆን በህዝብ የዕለት ተዕለት ህይወት (ህይወት ከተባለ) ውስጥ በእጅጉ ገዝፎ የምናየው መሪር ዕውነት ነው ። ታዲያ እንዲህ አይነቱን የገዥዎች ሥርዓተ መንግሥት በመሠረታዊ ዴሞክራሲያዊ የለውጥ ትግል ከማስወገድ ያነሰ አካሄድ እንዴት እናስብ?

10.ማህበራዊ ሥርዓታችን የተያያዘበት የመልካም መስተጋብር ድርና ማግ (fabric) ለሩብ ምዕተ ዓመት የጎሳ ማንነትን የፖለቲካ ሥልጣን መሠረታቸውና ማራዘሚያቸው ያደረጉ ጥቂት የገዥ ቡድኖች በሚያሳስብ ሁኔታ ማፈራረሳቸውን ቀጥለውበታል ።ከማላላት አልፎ ሊበጣጥሱት ተግተው መሥራታቸው ያስከተለውን አስከፊ ውጤት ዜጎች ለዘመናት ተዋደውና ተዋልደው ከኖሩበት የአገራቸው ክፍል መሬት በግፍ ሲባረሩ የታዘብነው መሪር ዕውነት ነው ። ማንኛውም ኢትዮጵያዊ በዜግነት መብቱ በየትኛውም የአገሩ አቅጣጫና አካባቢ በነፃነት ተዘዋውሮ በመሥራት የእራሱን ኑሮ የሚያሸንፍበትና አገሩንም የሚጠቅምበት ዕድል በጥቂት ጎሰኛ/ዘረኛ ገዥ ቡድኖች ለያይቶና አጋጭቶ የመግዛት ሥርዓተ መንግሥት ሲዘጋ ከማየት የበለጠ እንኳን እንደ ኢትዮጵያ ህዝብ የረዥም ጊዜ የአብሮነት ታሪክና ባህል ባለቤት ለሆነ ለየትኛውም አገር ህዝብ የሚከብድ ወይም ልብን ያደማል።

ይኸውና ከሰሞኑ ደግሞ ማየት ቀርቶ መስማት በሚከብድ ሁኔታ የሥልጣን ዕድሜያቸውን ያራዝምልናል በሚል በሶማሊ እና ኦሮሚያ ክልሎች ወገኖቻችን መካከል አነሳስተው የለኮሱትን ግጭት ወደ ለየለት መገዳደል (መተላለቅ) በመለወጥ እያደረሱት ያለው ዘግናኝ ጥፋት አብሮ የመኖር ማህበራዊና ባህላዊ እሴቶቻችን ምን ያህል አደጋ ላይ እንደወደቁ አግዝፎ የሚያሳየን እጅግ መሪር ዕውነት ነው።እናም ለዚህ ነው መሠረታዊ የዴሞክራሲዊ ለውጥ ካልሆነ በስተቀር ከዚህ የመከራና የውርደት ሥርዓተ መንግሥት ሌላ የሚያዋጣን (viable) መንገድ የለም ማለታችን የማያወላዳ ዕውነት የሚሆነው ።
11.ዛሬ የደረስንበት የሞራል (ጥሩውንና መጥፎውን የመለየትና የመምረጥ) ቀውስ እራሳችን ካላተለልን በስተቀር ከቁሳዊ ድህነታችን በላይ በእጅጉ የሚያሳስብ ነው ።
ዋሽቶና አታሎ የግል ጥቅምን ማርካት እንደ ነውር በማይታይበት ፥ በአንዱ ውድቀት ሌላው ስኬታማነቱን በሚለካበት ፥ አድርባይነትባይነት/ሙስና/ጉቦ የግል ወይም የቡድን ፍላጎትና ጥቅም ማስገኛና ማስጠበቂያ አይነተኛ መንገዶች በሆኑበት ፥ አገር ማለት በነፃነት ሠረቶ የሚኖርበት ሳይሆን በተገኘው አጋጣሚ ሁሉ አታሎና ዘርፎ የሚበለፅጉበት ሆኖ በሚታይበት ፥ ከገዥ ቡድኖች ጋር በጥቅም ሰንሰለት በመያያዝ የዘረፋ ሽርክና በተጧጧፈበት ፥ በአብሮነትና በዴሞክራሲያዊ ጀግንነት ታግሎ ነፃነት፣ ፍትህ ፣ ሰብአዊ ክብርና የጋራ ተጠቃሚነት በሰፈነባት አገር ውስጥ ከመኖር ይልቅ ሞትንና ከሞት የባሰ ውርደትና ሰቆቃን መርጦ መሰደድ በአስደንጋጭ ሁኔታ በሚስተዋልበት ሁኔታ ውስጥ መገኘታችን ከምር ልብ ካልነው የመሠረታዊና ዴሞክራሲዊ የሥርዓት ለውጥ አስፈላጊነት ነገ ሳይሆን ዛሬ መሆኑን ለመረዳት የእንተማመን ክርክር ውስጥ መግባት አያስፈልገንም።
12.የእምነት ተቋማት በረጅሙ የፖለቲካ ታሪካችን ሂደት በመሪዎች ደካማነት (የዓለማዊ ህይወት ፍላጎትን በመንፈሳዊ ካባ ጀቡኖ የማስኬድ) ፣ በምእመናን የሃይማታዊ እምነት መሠረታዊ ዕውቀት ጉድለት(illiteracy of religious beleifs) እና በገዥዎች ተፅዕኖ ምክንያት ከዓለማዊው የቤተ መንግሥት ፖለቲካ ተፅዕኖ ነፃ ሆነው ከተልኳቸው አኳያ <u>እንደተቋም</u> ለፍትህና ለሰብአዊ ክብር የታገሉበት አጋጣሚ ብዙም የሚያኩራራን አይመስለኝም።
በማይናወጡ የዕምነት መርሆዎችና እሴቶች ላይ ፀንቶ የመቆምና ለሚመጣና ለሚሄደው የፖለቲካ ሥርዓት ሁሉ አለመፍረክረክ ቢኖርማ ኖሮ በተለይ ብዙሃኑን የአገሪቱን ክርስቲያን ህዝብ የምትይዘው ቤተ ክርስቲያን በመፈንቅለ መንበረ ሥልጣን በሁለት የበላይ አመራር ተከፍላ ለአገርና ለወገን የአብሮነትና የፍቅር ፋና ወጊ ወይም መልካም አርአያ መሆን ባልተሳናት ነበር። በዕውነት ስለዕውነት እንነጋገር ካልን ከዚህ ሩብ ምዕተ ዓመት የወገን መከራና የአገራዊ ውርደት ሥርዓተ መንግሥት ያለመገላገላችን ምክንያት በፈጣሪ ማመካኘት ወይም የኢትዮጵያ ህዝብ በፈጣሪው አምሳል ከተፈጠረው ሁሉ ኅጢአተኛ የሆነ ይመስል “ካልተመለስክ ገና ፍዳህ ማለቂያ የለውም” የሚለውን የሰባኪዎቻችን ሰበካ ፈጣሪ እራሱ ሳይገርመው የሚቀር አይመስለኝም ። የኢትዮጵያ ህዝብ እንደማንኛውም ሰብአዊ ፍጡር ከኀጢያት የነፃ አይደለም ። ወደ ፊትም አይሆንም ። ይህን ማስተማርና ጥፋትን እንዲያርምና ላለመድገም ጥረት እንዲያደርግ የመምከር አስፈላጊነት ጥያቄ የለበትም ። ችግሩ ያለው ሰበካውንና ትምህርቱን ፣ ፀሎቱንና እግዚአታውን ፣ ሙብዓዉንና ምፅዋቱን ፣ ስግደቱንና አክፍሎቱን ፣ ቅዳሴውንና ምህላውን በወገን እየደረሰ ካለው መከራና ውርደት ጋር ወደ መሬት አውርዶ (ወደ ድርጊት ለውጦ) ከማሳየቱ ላይ ነው ። ስለክርስቶስ ስቅለትና ስለተከታዮቹ መስዋትነት ታሪክ ስንሰብክ ሰብአዊ ነፃነትና ክብር ፣ ፍትህና ርትዕ ፣ ፍቅርና ሰላም ፣ ደግነትና ቅንነት የሚያስከፍሉትን መተመን የማይቻል ዋጋ (priceless sacrifice) መዘከራችን ነው ። የሃይማኖት ወይም የቲዎሎጅ ተማሪም ባለዕውቀትም አይደለሁም። ነገር ግን የክርስቶስ

ተከታይ መሆን የቃለ ነቢብ ሊቅ የመሆንና እሱኑ ከህዝብ አደባባይ በስተጀርባ እየሰበኩ ይህን በማመን ብቻ ትድናላችሁ የምንለው ትክክል ስለመሆኑ አላነበብኩም ። ተግባር ስንል ደግሞ ማለቂያ ያጣውን የአገርና የወገን መከራና ውርደት በሚገኘው አጋጣሚ ሁሉ ማጋለጥና ማውገዝ ፣ እግዚአታና ጸሎት አስፈላጊነቱ እንዳለ ሆኖ ተግባር አልባ ሲሆን ግን ማደንቆሪያና ማስጠቂያ እንደሚሆን በድፍረት መመስከር እግዚአብሔር የሚወደው ስለመሆኑ በበኩሌ እምነቴ ፅኑዕ ነው ።

ይህ የሃይማኖት ተቋማት ውድቀት ለምን ይነሳል የሚሉ ወገኖቼ እንደሚኖሩና መብታቸውም እንደሆነ በሚገባ እረዳለሁ ። እንደኔ አረዳድ ግን አዲስ አበባ ላይ የቤተ ክርስቲያኗ "ቅዱስ እራስ (ሲኖዶስ)" ነኝ የሚለው አካል በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ የቤተ ክርስቲያኗ ተከታዮችና በአጣቃላይ ንፁሃን ዜጎች ይህን ያህል ዘመን የከፋ አገዛዝ ሰቆቃ ሰለባዎች ሲሆኑ በድፍረት ገዳዮችን መገሰፅ ቀርቶ የሰለባው ቤተሰቦችንና በአጠቃላይ ህዝብን እግዚአብሔር ያፅናችሁ ያላለ ይኸውና ህዝቡ በቃኝ ብሎ በተነሳ ቁጥር በሽምግልና እና በሰላም ተልኮ ስም የገዳይ ገዥዎችን ዕድሜ ለማራዘም ሽር ጉዱን መግለጫ በማውጣት ጀምሯል ። መግለጫው ደግሞ በይዘቱ ከመንግሥት ቤተ መንግሥት ወይም ከህወሃት/ኢህአዴግ ጽ/ቤት የተቀዳ ለመሆኑ ጥርጥር የለውም ። ታዲያ ይህን "ቅዱስ አካል" መውቀስ እስከሃጢአት የሚደርስ ነገር ነው ለሚሉ ወገኖቼ ያለኝ መልስ የወገንና የአገር መከራና ውርደት ግድከማይላቸው ጋር የሚወዳጅ ጨካኝ አምላክ ፈፅሞ የለምና ስለ እኔ ወይም ሃሳቤን ሊጋሩ ስለሚችሉ ወገኖቼሃጢያተኝነት አትጨነቁ የሚል ነው ።

በነገራችን ላይ የውድቀቱን ደረጃ በማነፃፀር የአዲስ አበባው ላይ ትችቴን ሰነዘርኩኝ እንጅ ወዲህ ውቅያኖስ ማዶ ያለውም በአገርና በወገን ላይ እየደረሰ ካለው መከራና ውርደት አስከፊነት አንፃር ሲፈተሽ በውጭ ለሚገኘው አማኝ እና በአጠቃላይ ኢትዮጵያዊያን የመሰባሰብና የአብሮነት አርአያ የመሆኑ ነገር ብዙም የተሳካለት አይደለም ። እንደ ተቋም ማለቴ ነው ።

እናም ዴሞክራሲያዊ የሥርዓት ለውጥ በተለይ እንደኛ ባለ እጅግ አብዛኛው ህዝብ ከሃይማኖት (ተቋማት) ጋር በአንፃራዊ መልኩ የጠበቀ ግኑኙነት ባለበት አገር የተቋማቱ መሪዎች ብቻ ሳይሆኑ የሰባኪያን (መምህራን) እና የቀሳውስት ሚና የጎላ ነው። ህዝብ ለነፃነቱ ፣ ለሰብአዊ መብቱ ፣ ለሰብአዊ ክብሩ ፣ ለፍትህ ፣ ለአብሮነት ፣ ለእኩልነት ፣ ለሰላም ፣ ለፍቅርና ለጋራ ብልፅግና በአንድነትና በፅናት እንዲቆም ከሃይማኖት መሠረታዊ እምነት፣ መርህና ሥነ ምግባር ጋር በማያያዝ ወይም በማገናኘት የሚሰብኩበትን ዘዴ (methodology) የመቀየሱ አስፈላጊነት አሁን ላለንበት ሁኔታ ብቻ ሳይሆን ከድል በኋላ ለሚመሠረተው ህዝባዊ ሥርዓት መጠናከርና ስኬታማነት የሚኖረው አስተዋፅኦ ከፍተኛ ነውና ከምር ልናስብበት ይገባል የሚል የፀና እምነት አለኝ ።

ያለዚያ ፖለቲከኞች አይደለንም የሚለው የተለመደና ልፍፍስ ምክንያት ከተሰጠን "ህዝቤን ጠብቁ" ትዕዛዝ ጋር የሚገናኝ ሳይሆን ዝም ብለን ሽምድደን በዘልማድ የምናነበንበው ቃለ ነቢብ ነው የሚሆነው። "አይ ህዝቤን ጠብቁ ማለት እኮ ከኀጢት ነው" ሊባል እንደሚችል እረዳለሁ ። የሚኖረኝ ምላሽ አዎ! የሚል ይሆንና ግን እኮ የኀጢአቱ ምንጭ ግፈኛ ገዥዎችና ፣ደጋፊዎቻቸው እና የህዝብን መከራ በህዝብ አደባባይ ወይም በሌላ በማነኛውም አመች ጊዜና ሥፍራ ቀድሞ በመድረስ የክርስቶስን አርአያ ፈጽሞ የማይገኝ የሃይማኖት መሪ ወይም ሰባኪ ወይም ካህን እንጅ መከረኛው ህዝብ እንዴት ይሆንል? የሚል ነው ። ሰውን ማሰቃየት ፣ ማዋረድ ፣ ያለኀጢአቱ ማሰርና መግደል ኀጢአት ነወና በህግ አምላክ መባል ያለበት ህዝብን ቁም ስቁሉን የሚሳየው ነው ወይስ የኀጢአተኞች ሰለባ የሆነው ህዝበ አዳምና ሔዋን ? ነፃነቴን ብሎ ከገዳይ ኀጢአተኞች ጋር የሚፋለመው ነው ወይስ ቤተ እምነትን ከገሃዱ ዓለም (መከራውና ውርደቱ ከሚካሄድበት ) መሸሻና መደበቂያ ያደረገው የሃይማኖት መሪ ወይም ሰባኪ ? ብዙ መጠያየቅ ይቻላል ።ግን የእስካሁኑ በቅቶ ወደ ትክክለኛው መንገድ መምጣትና የወደፊቱን የጋራ እጣ ፈንታችን በጋራ ዕውን ማድረግና በሰላምና በፍቅር መኖሩ ከመንም በላይ ይበጀናልና ወደ ዚያው እንለፍ ።

ሃሳቤንና አስተያየቴን ላጠቃለው ፥

አዎ! የዛሬ ገዥዎቻችን የተነሱበት ፍልስፍና እና አስተሳሰብ ፣ የአደረጃጀታቸው ቅርፅና ይዘት ፣ የትግል ተልኮአቸው መነሻና መዳረሻ እንኳን ለመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ቀርቶ በቀጥታ ተወልደንብሃልና በጉያህ ውስጥ አድገንብሃል ለሚሉት የአቶ መለስን ቃል ልዋስና «ወርቅ» ሕዝብም ለፖለቲካ ፍጆታቸው ሲሉ ከሌላው ወገኑ ጋር አላስፈላጊ ጥላቻ ውስጥ ሊዘፍቁት ከመሞከር በስተቀር እንደ ሕዝብ የፈየዱለት በጎ ነገር የለም። በእነዚህ ዥዎቻችን ተፀንሶ በተወለደ፣ በሸር እና በሴራ በተተከለ፣ የሦሥቱንም የመንግሥት አካላት (legislative, executive and judiciary) ሥልጣንና ተግባር ጠቅልሎ በያዘው የአስፈፃሚው አካል (executive branch) ቁጥጥር ሥር በወደቀ እና ውርደትና መከራ በቃኝ በማለት የነፃነት ፣ የፍትህ ፣ የእኩልነት ፣ የአብሮነት ፣ የሰብአዊ መብት እና የጋራ ብልፅግና ሥርዓትን ዕውን ለማድረግ የሚነሳውን የህዝብ ንቅናቄ ለመጨፍለቅ በተዘጋጀ የጦርና የፀጥታ ኀይል ሳይቀር አዝምተው እኔን ያየህ ተቀጣ እያሰኙ ዙፋናቸውን አይደፈሬ ለማድረግ ሞክረዋል። በጫካኝ የአፈና ኀይል እና ድምፅ በሌለው የስለላ መረብ (ጥላ ወጊ) እየታገዘ

ለሩብ ምዕተ ዓመት የዘለቀው ሥርዓተ መንግሥት ነገ ሳይሆን ዛሬ በቃ! ካልተባለ አገርንና ህዝብ እየወረዱበት ያለው ቁልቁለት በእጅጉ ያሳስባል፡፡፡

በቃ ለማለት ደግሞ የሥርዓትን ምንነት ፣ እንዴትነት እና ወዴትነት ከመረዳት አልፈን የየራሳችንን ምንነት፣ ማንነት ፣ ለምንነት ፣ እንዴትነት እና ወዴትነት መጠየቅና እንደግለሰብም ሆነ እንደማህበረሰብ በነፃነት ፣በፍትህ፣ በእኩልነት ፣በጋራ ብልፅግና እና በሰላም የሚያስተናግደንን (የሚያኖረንን) ሥርዓተ ማህበረሰብ መጀመሪያ በትክክል ጠንቅቀን ማወቅ፣ ከምር መፈለግ እና ብሎም ዕውን ለማድረግ አስፈላጊው መስዋዕትነት በሚከፈልበት የትግል መስክ የምንችለውን ሁሉ ለማድረግ ለየራሳችን ቃል መግባት የግድ ከሚለን ጊዜና ሁኔታ ላይ የምንገኝ መሆኑን ከምር አምነን መቀበል አለብን ፡፡

አዎ! ለተሻለ የሥርዓት ለውጥ በተለይም ለሕዝባዊና ዴሞክራሲያዊ ለውጥ የሚደረግ ትግል ስንል ስፋቱና ጥልቀቱ ለብዙ ዘመናት የዘወትር ፀሎት እስኪመስል ድረስ ከምንደጋግመው «የሥርዓት ይለውጥ!» መፈክር አልፎ የሚሄድ እና በዚያው ልክም የአርበኝነትና የጀግንነት ውሎን (patriotic and heroic engagement) ግድ የሚል መሆኑን ከምር የመረዳትንና ሆኖ የመገኘትን አይታለፌነት ወደን መቀበል አለብን። ታዲያ ነገ ሳይሆን ዛሬ መሆን ያለበት። ይህን እንድናደርግና መሆን ያለብንን ሆነን እንገኝ ዘንድ ለአያሌ ዘመናት እና በተለይም እስከአሁን »እየኖርንበት» ካለነው የሩብ ምዕተ ዓመት የፖለቲካ ደዌ ለመገላገል ማድረግ የነበረብንን ባለማድረጋችንና ሆነን መገኘት የነበረብንን ሆነን ባለመገኘታችን እንደ ህዝብና እንደአገር የወረድንበት የመከራ ቁልቁለት በቁጭት ሊያነሳሳንና የሰቆቃውን ዘመን ለማሳጠር ኀይል ሊሆነን ይገባል።

ታዲያ ይኸ ቁጭት (ተገቢ ፀፀት) ከመጣንበት መብትና ነፃነት አልባ የፖለቲካ ታሪካችን እና በአሁኑ ወቅትም «እኛ ያላዘዝንበትና ያለገደብ ያልመዘበርነው አገር ፍርስርሱ ይውጣ» የሚሉ ገዥ ቡድኖች ካዋቀሩት ፣ ከዘረጉትና ከተቆጣጠሩት ሥርዓተ አገዛዝ እንወጣ ዘንድ ኢጋዥ ኀይል እንጅ መቆዘሚያ መሆን የለበትም።